**Ethiopian Journal of Business and Social Science**

**DOI:** https://doi.org/10.59122/ EJBSS674

**Volume: 8 Number: 2, 2025, Pages: 155-179**

**ISSN: 2707-2770**

# የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች አገነባብ ትንተና በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራ ልማድ

**Atsede Yaregal Fente[1*], Guday Emire Kassahun[2], Watenigus Mekonnen[1]**

[1]Bahir Dar University,
[2]Addis Ababa University
[*]Crosponding auther: Email: atsemill@yahoo.com

***Article Info***

*Accepted on:*
*October, 2025*
*Published on:*
*December, 2025*

***©Arba Minch University, all rights reserved***

## *አጠቃሎ*

*ይህ ጥናት “የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች አገነባብ ትንተና በዶርዜ ማኅበረሰብ የጋብቻ ከበራ ልማድ” በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የዶርዜ ማኅበረሰብን የጋብቻ ከበራ ልማድ ከሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች አገነባብ አንጻር መመርመር ሲሆን፤ በጋብቻ ሥኑ-ስርዓቱ ውስጥ የሴቶችን እና የወንዶችን ተግባራት መለየት፤ እና በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ የሚከወኑ ልማዶች እና ትዕምርቶች ለስርዓተ-ፆታ አገነባብ ያላቸውን አንድምታ ማብራራት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን አካቷል። እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የመስክ መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት እና በምልከታ ዘዴዎች ተሰብስበዋል። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ሥነዘዴን በመከተል እና ኢትኖግራፊያዊ የምርምር ስልትን በመተግበር የመስክ መረጃዎች በይዘት ተደራጅተዋል። እነዚህ መረጃዎች በማኅበራዊ ሚና (Social Role Theory) እና በትዕምርታዊ መስተጋብር (Symbolic Interactionism) ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ በገላጭ እና በትርጓሜ (Interpretive) ስልት ተተንትነዋል። በትንታኔው መሰረትም፤ የዶርዜ ማህበረሰብ በሚከውናቸው የጋብቻ ከበራዎች ውስጥ ፆታን መሰረት ባደረጉ ተግባራት እና ትዕምርቶች የታጀቡ ናቸው።በዚህም መሰረት፤ በከበራዎቹ ውስጥ ወንዶች የስርዓት መሪ፣ ፈፃሚ እና አቅራቢ፤ ሴቶች ደግሞ አሰናጅ እና ደጋፊ ሆነው ቀርበዋል ። በእነዚህ ከበራዎች ውስጥ ጎልተው በታዩ ዘር የመተካት፣ ውሳኔ የመስጠት፣ የታዛዥነት እና አክባሪነት እንዲሁም የመንከባከብ ይዘቶች ውስጥ ወንድነት እና ሴትነት በተለያየ መልክ መታዬታቸውን ጥናቱ አረጋግጧል። በዚህም በአብዛኛው ወንዶች የመሪነት፣ የውሳኔ ሰጪነት እና የአቅራቢነት ሚናቸው ጎልቶ ሲታይ፣ ሴቶች ደግሞ የተንከባካቢነት እና የደጋፊነት ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።*

***ቁልፍ ቃላት፡-*** ስርዓተ-ፆታ፣ የስርዓተ-ፆታ ሚና፣ ጋብቻ፣ ከበራ እና ልማድ፣ ዶርዜ

## 1. መግቢያ

ስርዓተ-ፆታ ብዙ ገጽታዎችን ያቀፈ በይነዲሲፒሊናዊ ዘርፍ ነው። ይህ መስክ ምንም እንኳን እንደ ፅንሰ-ሃሳብ ራሱን ችሎ የቆመው በ1970ዎቹ ቢሆንም፣ እንደ ርዕሰ ጉዳይ መታየት የጀመረው ከ20ኛው መቶ

ክፍለ ዘመን መባቻ አንስቶ እንደሆነ ጸሐፍት ያስረዳሉ (Kousaleous, 1999; Pilcher & Whelehan, 2004; Sawin 2004)። በዚህም ምክንያት በጥናት ታሪኩ ውስጥ የተለያዩ እሳቤዎችና የጥናት ትኩረቶች መነሳታቸው ይነገራል። እነዚህ ጥናቶች እንደ ዘመን ቅደም ተከተላቸው በተፈጥሮ፣ በስነ-ልቡና፣ በማኅበረሰብ እና በመዋቅር ላይ ያተኩራሉ። በስርዓተ-ፆታ እሳቤ ውስጥ ጎልቶ ከሚታዩ ጉዳዮች ውስጥ ዋናው የስርዓተ-ፆታ ሚና ነው።

ሚና ከአንድ ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚጠበቅና ድርሻን ከመወጣት ጋር የሚያያዝ ጠባይን ያመለክታል። እንደ Turner (2002) ሐሳብ፣ ሚና ከአንድ ማንነት ወይም ማኅበራዊ ደረጃ ጋር የተሳሰረ የባህርይና የአመለካከት ቅጥ ሲሆን ማኅበራዊ እውቅና ያለውና በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድም ታውቆ የሚከወን ነው። እነዚህ ማኅበራዊ ደንቦችም በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የሰዎችን ባህርይ የሚመሩ የጋራ ሕጎችን መሠረት ያደረጉ እንደሆኑ ይገለጻል(Lindsey, 2016)። ባህላዊ ደንቦች በእያንዳንዱ ደረጃ ያለንን መብትና ግዴታ ይወስናሉ። ከዚህም የተነሳ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አባል እንደ ዕድሜ ደረጃው፣ እንደ ፆታው እና እንደ ማኅበራዊ ደረጃው መሠረት የሚጠበቅባቸው የተለያዩ መደበኛ ሚናዎች አሉት (Lindsey, 2016)።

የስርዓተ-ፆታ ሚና አንድ ማህበረሰብ ለእያንዳንዱ ፆታ የሚሰጣቸውን ተግባራት፣ ከዚህም ጋር ተያይዘው የሚጠበቁትን አመለካከቶች እንዲሁም ጠባያትን የሚያካትት ሐሳብ ነው። ይህንን መሠረት በማድረግ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ፆታዊ የሥራ ክፍፍል በዚህ ሐሳብ ውስጥ የሚገኝ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። በWood እና Eagly (2000) ሐሳብ መሠረት፣ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች በማህበረሰቡ የሥራ ክፍፍል ልማድና ማኅበራዊ ሚናዎች ውስጥ ሰርፀው የሚገኙ ናቸው። ይህም ከስርዓተ-ፆታ ሚና ጋር ተያይዘው ለሚመጡ አመለካከቶች በር ከፋች እንዲሆን ማድረጉን Wood እና Eagly (2012) ይገልፃሉ ።

ለስርዓተ-ፆታ ሚና ህልውና ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ደግሞ ፆታዊ የሥራ ክፍፍል ነው። ፆታዊ የሥራ ክፍፍል እንደ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ የተለየ ትኩረት ማግኘት የጀመረው ለጋብቻ እና ለማህበራዊ ተቋማት መገንባት ዋነኛ ምክንያት በመሆኑ እንደሆነ ይገለጻል (Burton et al., 1970)። ፆታን መሠረት ባደረገው የሥራ ክፍፍል ውስጥ ለሚናዎች መለያየት መሠረታዊ ምክንያቶች ናቸው ተብለው የሚጠቀሱ መላምቶች ከ1930ዎቹ ጀምሮ በተለያዩ ተመራማሪዎች ሲቀርቡ ቆይተዋል (Alesina et al., 2013; Brown 1970; Burton et al., 1970; Eagly et al., 2000)። እነዚህ መላምቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ለስርዓተ-ፆታ ሚናዎች መለያየት መነሻው ተፈጥሯዊው የፆታ ልዩነት ነው ብሎ በማመን የሚነሳው የስነ-ህይወታዊ መላምት ሲሆን፣ የልዩነቱን መሠረትም ከሴቶች የመውለድ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች እና ከወንዶች በአካላዊ መጠን መግዘፍና ጥንካሬ አንፃር በማድረግ ይመረምራል (Eagly et al., 2000)። ይኸውም በተለይ በቀደምት አጥኚዎች ተንጸባርቋል (Brown 1970; Burton et al., 1970)። እነዚህ ምሁራን ፆታዊ የሥራ ክፍፍልን በሚመለከት ባነሷቸው ሐሳቦች ወንድ ባለው ከፍተኛ የአካል ጥንካሬ ምክንያት አድካሚ የሆኑ ሥራዎችን ማከናወን እንደሚችል ይገልጻሉ። በተቃራኒው ሴት ከተፈጥሯዊ የሴትነት ግዴታዋ ጋር በተያያዘ አድካሚ የሆኑና አካላዊ ጥንካሬን የሚጠይቁ ሥራዎችን መሥራት እንደማትችል እንዲሁም ከእናትነቷ የተነሳ ከቤቷ ርቃ መሥራት እንደማትችል ይገልጻሉ። ሴቶች ውጤታማ ናቸው ተብሎ የሚታሰበው ሥራው ከቤት የማያርቅ፣ ለብቻ ሊሠራ የሚችልና ጥልቅ ትኩረትን የማይጠይቅ፣ ለአደጋ የማያጋልጥና ሊቋረጥ በሚችል ሁኔታ ውስጥ ሊሠራ የሚችል ሲሆን ነው (Brown, 1970; Burton et al., 1977)።

በመሆኑም በዚህ እሳቤ አራማጆች እምነት የስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎች መለያየት መሠረታዊው ምክንያት ተፈጥሯዊ ገጽታ ነው።

ሌላው ከስርዓተ-ፆታ ሚና መለያየት ጋር ተያይዞ በሁለተኛነት የሚነሳው መላምት ባህልን መሰረት ያደረገው ባህል ተኮር (Cultural Determinism) ነው። ሰዎች የሚኖሩበት አካባቢ፣ ባህል እና ማህበረ- ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ለሚናዎች መለያየት ምክንያት እንደሆኑ የሚጠቅስ ማህበረ-ባህላዊ እሳቤ ነው (Ickes, 1993)። በመሆኑም፣ ባህላዊ የሆኑ ስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎች በተፈጠሩበት ማህበረሰብ ባህል ነክ እምነቶች፣ ተቋማት እና ክዋኔዎች ውስጥ ስር ሰደው የሚኖሩ እና የሚፈጠሩ መሆናቸውን Sidanius እና ሌሎችን (1991) በመጥቀስ Ickes(1993) ያስረዳሉ።

ከላይ የቀረቡ መላምቶችን በማጣመር ቀጥሎ የተነሳው ደግሞ የባዮማህበራዊ(Biosocial) መላምት ነው። እንደ Wood and Eagly (2012) ያሉ ምሁራን፣ ተፈጥሯዊ ከሆኑ የፆታ ጉዳዮች በተጨማሪ ሰዎች የሚኖሩበት አካባቢ፣ ባህል እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በፆታዊ የስራ ክፍፍል ውስጥ ለሚመጣው የፆታ ሚና የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው ይገልጻሉ። ሁለቱም መሰረታዊ ምክንያቶች በመሆናቸው የፆታ ሚናው በማህበረሰቡ የሚገነባ መሆኑንና ይኸን ልማድ የሚያፀኑ መንገዶችን እንደሚፈጠሩ ያነሳሉ። ይህ ማለት የፆታ ሚናዎች ማህበረሰቡ በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚጥላቸው የባህሪ፣ የአመለካከት እና የኃላፊነት መመዘኛዎች ውጤት ናቸው። የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች በስነህይወታዊ እና ማህበራዊ ኃይሎች መካከል የሚፈጠሩ ውስብስብ መስተጋብሮች ውጤት እንደሆኑ ደግሞ Wienclaw (2011) ይጠቅሳሉ። ስርዓተ-ፆታ በባዮሎጂያዊ ባህሪያት ብቻ ሳይሆን በምንኖርበት ማህበረሰብ እና ባህልም ጭምር የተገነባ ነው። ይህም የፆታ ማንነት እና ሚናን ውስብስብ እና ተለዋዋጭ ያደርገዋል። በመሆኑም፣ ተፈጥሯዊ ገፅታ ላይ በመንተራስ የሚመሰረተው ማህበረ-ባህላዊውን ሥርዓትም አንድ ግለሰብ የሚጠበቅበትን እንዲያውቅ፣ እንዲያምን እና ራስን በዚያ ስርዓት ውስጥ እንዲያስገዛ ያደርገዋል። ይህም ግለሰቦች ስለ ስርዓተ-ፆታ ተገቢነት ያላቸውን እምነቶች እንዲቀበሉ እና ማህበረሰቡ ከነሱ የሚጠብቀውን እንዲፈጽሙ ያደርጋል፤ ሂደቱም የፆታ ሚናዎችን ለማጠናከር እና ለማስቀጠል አስተዋፅኦ ያደርጋል። በመሆኑም፣ ይህ መላምት የስርዓተ-ፆታ ሚና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚያይ መሆኑ እንዲሁም የስርዓተ-ፆታ ሚናን አገነባብ፣ ተስተላልፎ እና ለውጥ እንዴትነት ለማየት አይነተኛ ሆኖ በመገኘቱ ጥናቱ በዚህ መላምት ይቃኛል።

ከስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ አመለካከቶች እና እምነቶች ከወንድነትና ከሴትነት ጋር በተያያዘ ላሉ አመለካከቶች፣ እምነቶችና ባህሪያት መስፋፋትና መተላለፍ ላይ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። እነዚህ አመለካከቶችም በአብዛኛው በማህበረሰብ ዘንድ ተመሳሳይነት አላቸው። በልማዳዊ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ወንዶች የገቢ አመንጪነት (Breadwinner)፣ ሴቶች ደግሞ የተንከባካቢነት (Homemaker) ሚናዎችን እና እነዚህን ሚናዎች መወጣት በሚያስችሏቸው የሥራ ድርሻዎች ላይ ይሳተፋሉ። ይኸም ወንዶች ግብ ተኮር (Instrumental)፣ ሴቶች ደግሞ ስሜት ተኮር (Expressive) ባህሪያትን እንዲላበሱ እንደሚያደርግ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ (Eagly et al., 2000; Wienclaw, 2011; Eisenchlas, 2013)። ልማዳዊ የሆነው የስርዓተ-ፆታ ሚና የሚቀዳው ከማህበረሰቡ ፆታዊ የስራ ክፍፍል መሆኑን በሚገልፀው የ Eagly ማህበራዊ ሚና ንድፈሃሳብም ልማዳዊ የስርኣተ-ፆታ ሚና በሚገኝባቸው አካባቢዎች ወንዶችን እንደ አቅራቢ ሴቶች ደግሞ እንደ ተንከባካቢ ማየቱ የተለመደ እንደሆነ ይጠቁማል (Eagly et al., 2000)። እነዚህ ሚናዎችም የተለያዩ መገለጫዎች ያሏቸው ሲሆን የተንከባካቢነት ሚና ከትህትና፣ ከማገዝና ከመንከባከብ፤ የገቢ

አመንጪነት ሚና ደግሞ ከተወዳዳሪነት፣ ከራስ መቻል፣ በዓላማ ከመጽናትና ከመሪነት ብቃት መኖር ጋር ተያይዞ እንደሚታይ ይገለጻል (Blakemore et al., 2009)፡፡

የስርዓተ-ፆታን ጉዳይ የሚመለከቱ ፖሊሲዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ከመተግበራቸው በፊት የስርዓተ-ፆታ ልማድ ልዩነቶችን መነሻ ከሥር መሠረታቸው ማየት እንዲሁም ያለፉባቸውን ውስብስብ ሂደቶች መረዳት ያስፈልጋል (Giulian, 2020)። ከዚህ በመነሳትም ፖሊሲዎች ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ ብቻ ሳይሆኑ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ መካከል ያለውን የባህል ልዩነትም በሚገባ ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸውም ያክላሉ። ለዚህም የማኅበረሰቡን የስርዓተ-ፆታዊ ሚና አገነባብ ባህሉን ባማከለ መልኩ ማጥናት አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የሰው ልጅ ስርዓተ ዓለሙን ከሚገነዘብባቸው፣ ከሚቀርጽባቸውና ከሚገነባባቸው ጉዳዮች መካከል ስርዓተ ከበራዎች ይገኛሉ። ከበራዎች የሰው ልጅ ሕይወትን እንዲገነዘብ የሚያደርጉ ቋሚ ሰነዶች መሆናቸውን (Frobish, 2004) ያስረዳሉ። ስርዓተ-ፆታን በመገንባት፣ በማስታወስና በማጽናት ረገድ ከበራዎች ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች በተሻለ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው የሚጠቅሱት Pollock(2004)፤ ከበራዎች ሁሉም በሚባል ደረጃ ሥርዓተ-ፆታዊ እንደሆኑ ይገልጻሉ። በተመሳሳይም ስርዓተ-ፆታ እና ከበራዎች የሰውን አተያይ በመቅረፅ ረገድ ትስስር እንዳላቸው Naik እና Sethi (2025) ይጠቅሳሉ። ከበራዎች ቃላዊ፣ ድርጊታዊ እና ቁሳዊ ገፅታዎች ተሰናስለው የሚገኙባቸው እና ማህበረ-ባህላዊ ዳራው በሰፊው የሚስተዋልበት እንደመሆኑ ማህበራዊ እሳቤን ለመረዳት እና ለማግኘት ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው። በአብዛኛው ማህበረሰብ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ አይቀሬ የሚባሉት የህይወት ክስተቶችን ተከትለው ከሚመጡ ከበራዎች ውስጥ ውልደት፣ ጋብቻ እና ሞትን የሚመለከቱት ዋናዎቹ ናቸው (Bell, 1997)፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ይህ ጥናት በጋብቻ ከበራዎች ላይ ያተኩራል። የጋብቻ ከበራዎች የስርዓተ-ፆታ ሚናዎችን በሚገልጡ እና በሚገነቡ ትዕምርቶች የበለፀጉ እንደመሆናቸው የተጠኚውን ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚና አገነባብ ለማሳየት አይነተኛ የፎክሎር ቅንጣት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች አሰጣጥም ሆነ አገነባብ ከፆታዊ የስራ ክፍፍል ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ሲሆን፣ ይህን ጉዳይ ከባህላዊ ስርዓቶች ጋር አስተሳስሮ የተሰራ ጥናት አለመገኘቱ  ለዚህ ምርምር መነሻ ምክንያት ነው፡፡ የስርዓተ-ፆታ ሚና አሰጣጥ እና ስሪት በተለይ የተለያዩ የሙያ መስኮች በስብጥር በሚገኙባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ጥብቅ እና ውስብስብ መሆኑ ይነገራል፡፡ እንደዚህ አይነት የሙያ ስብጥሮች ከሚገኙባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የዶርዜ ማህበረሰብ አንዱ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በዋናነት በሽመና ስራ በኢትዮጵያ ደረጃ ስማቸው ከገነኑ የሙያ ባለቤቶች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ማህበረሰብ ነው (Mathiszig 2015)፡፡ ከዚህ የሙያ መስክ በተጨማሪም ማህበረሰቡ በእርሻም የሚተዳደር ሲሆን የሸክላ፣ የቆዳ እና የብረት ስራዎችም በተወሰነ መልኩ የሚገኙበት መሆኑ የሙያ ስብጥሩን ከፍ ያደርጉታል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ከእርሻ ስራ በተጨማሪ የሽመና ስራንም እንደ መተዳደሪያ የሚጠቀም መሆኑ የስርዓተ ፆታ ሚናውን ቅጥ (pattern) ለማየት አመቺ ያደርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማህበረሰቡ ፆታዊ የስራ ጥብቅ እና ውስብስብ መሆኑ ተጠቅሷል (Getaneh, 2004; Mamo & Getaneh, 2022; Olmstead, 1975)፡፡

በ19ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ የዶርዜ ማህበረሰብ የሚገኝበትን የጋሞ ደጋማ አካባቢ ወደ ሀገሪቱ ማዕከላዊ መንግስት ስር መጠቃለሉ፤ በማህበረሰቡ ዘንድ ያመጣው ለውጥ እንዳለ አጥኚዎች ይገልፃሉ (Freeman, 2002; Getaneh, 2004; Olmstead, 1975)፡፡ ይህን ሁኔታም በተለይ የሽመና ሙያ ለነበራቸው የዶርዜ

አካባቢ ወንዶች ወደ አዲስ አበባ በመሄድ የነበራቸውን የሽመና ልምድ የመተግበር እድልን ፈጥሮላቸዋል። ይህም ከዚያን ዘመን በኋላ በስፋት ለተስተዋለው የወንዶች ወደ ከተማ ፍልሰት በር ከፋች ምክንያት ሆኗል። እንደዚህ አይነት ክስተቶች ደግሞ የአካባቢውን የፆታ ስብጥር በእጅጉ እንደቀየሩት መረጃዎች ያሳያሉ(Getaneh, 2004; Olmstead, 1975)።ይሁን እንጂ የማህበረሰቡ ፆታዊ የስራ ክፍፍል ከዚህ ክስትተ በኋላም በጥብቅ ይተገበራል።

የዶርዜ ማህበረሰብን የሚመለከቱ በርካታ ጥናቶች ይገኛሉ። የእነዚህ ጥናቶች ትኩረትም ምጣኔ ሃብታዊ ገጽታ (Halperine & Olmstead, 1976)፣ የሴቶች ሚና እና ምጣኔ ሃብታዊ ገጽታ (Olmstead, 1975; Getaneh, 2004)፣ የሽመና ልማዱ (Mathiszig, 2015)፣ ባህላዊ መድሃኒት (Wagaye, 2016)፣ የቤት አሰራር (Olmstead, 1972) እና የሴቶች ፆታዊ መብቶች ከባህሉ እና ህጋዊ አሰራሩ አንፃር (Getaneh, 2016) ናቸው። ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ስርዓተ-ፆታዊ ጉዳዮችን ያነሱት የJudith Olmstead (1975) እና የGetaneh Mehari (2004 & 2016) ጥናቶች ናቸው። Judith Olmstead (1975) የዶርዜ ሴቶች እና የአጎራባቹ የዲታ አካባቢ ሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በሚመለከተው በቀረበው የOlmstead (1975) ንፅፅራዊ ጥናት፣ በሁለቱ ማህበረሰቦች ዘንድ ያለውን የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ተብራርቷል። በጥናቱ መሰረት፣ በወቅቱ የዶርዜ ሴቶች ባሎቻቸው ለሽመና ወደሌሎች አካባቢዎች ስለሚሄዱ፣ በቤት ውስጥ ያለው የስራ ጫና በእነሱ ላይ ይበዛል። ከዚህም የተነሳ ኑሯቸውን ለመደገፍ ከተጎራባች አካባቢ ሴቶች ይልቅ በገቢ ማምንጫ ስራዎች ውስጥ እንደሚሳተፉ በጥናቱ ተብራርቷል።ይህ ሃሳብ የሴቶች ሚና በቤተሰብ ኢኮኖሚ ላይ ያለውን አስተዋፅዖ በሚቃኘው የGetaneh(2004) ጥናትም ተነስቷል።የወንዶች ፍልሰት በዶርዜ ማህበረሰብ የቤተሰብ መዋቅር ገፅታ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን በመቀየሩ ምክንያት በሴቶች ሚና ላይ ተፅዕኖ ስለማሳደሩ በጥናቱ ተብራቷል። የዶርዜ ሴቶች ምንም እንኳን በርካታ የስራ ጫናዎች ቢኖርባቸውም፣ ማህበረሰቡ በሚከተለው ጥብቅ አባዊ ርዕዮተዓለም የተነሳ ወንዶች የኢኮኖሚ ሁኔታ ብልጫ እና የባለቤትነት መብት እንዳላቸው በጥናቶቹ ተጠቅሷል(Olmstead, 1975; Getaneh, 2004)። ከእነዚህ ጥናቶች በተጨማሪም Getaneh(2016) የሴቶችን ፆታዊ መብቶች ከባህላዊ ተቋማት፣ ከህጋዊ የፍትህ ተቋማት እና ሰብዓዊ መብት መርሆች አንፃር የተፈተሸበት ጥናት ቀርቧል። በዚህ ጥናት ማህበረሰቡ የሚገለገልበት የነውር ደንብ(ጎሜ) እና ተያያዥ ባህላዊ ተቋማት የሴቶችን ፆታዊ መብት(Sexual right) የሚያስጠብቁም እንደዬ ሁኔታው ደግሞ የሚነጥቁም ሆነው መገኘታቸው ታይቷል። ይህም ደንቦቹ በዋናነት በቦታ እና በጊዜ ማህቀፍ ውስጥ የሚተረጎሙ በመሆናቸው በተመሳሳይ መልኩ እንዳይተገበሩ ማድረጉ ተጠቅሷል።

በአጠቃላይ እነዚህ ጥናቶች የሴቶችን ሚና ከምጣኔ ሃብታዊ ገፅታ አንፃር ከማየት በዘለለ ሚናዎቹ የሚገለፁባቸውን ባህላዊ ገጽታዎች በመመርመር የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ ሚና እሳቤን በማሳየትና በመገንበት ረገድ የምርምር ክፍተት እንዳለ መገንዘብ ተችሏል።በመሆኑም ይህ ጥናት የዶርዜ ማኅበረሰብን የጋብቻ ከበራ ልማድ መነሻ በማድረግ ከሥርዓተ-ፆታ ሚና አገነባብ አንጻር ምን አይነት ይዘትና ተግባር እንዳለው በመመርመር፤ የጥናት ክፍተትን ይሞላል ተብሎ ይታመናል።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም የዶርዜ ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎችን በጋብቻ በከበራዎች አማካኝነት በመመርመር የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ እሳቤ መተንተን ነው። የሚከተሉት ደግሞ ንዑሳን ዓላማዎቹ ናቸው።

1. በጋብቻ ሥነ-ስርዓቱ ውስጥ የሴቶችን እና የወንዶችን ተግባራት መለየት፤
2. በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ የሚከወኑ ልማዶች እና ትዕምርቶች ለስርዓተ-ፆታ አገነባብ ያላቸውን አንድምታ ማብራራት

## 2. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የስርዓተ-ፆታ ሚናዎችን በጋብቻ በከበራዎች አማካኝነት የሚመረምር ነው፡፡ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በጥልቀት ለማግኘት፣ ለመረዳት፣ ለመግለጥ ወይም ለማብራራት ያመች ዘንድ ዓይነታዊ የምርምር አይነትን በመከተል በኢትኖግራፊዊ የምርምር ስልት ተቃኝቷል፡፡

### የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይ እና ካዕላይ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ከቀዳማይ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት እና በምልከታ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመጀመሪያው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የምልከታ ዘዴ ሲሆን በአራት ዙር ተካሂዷል፡፡ ይህም በዋናነት ጋብቻን ተከትለው በሚመጡ ስርዓቶች እና በመስቀል በዓል ስርዓቶች ላይ ተሳታፊ እና ከፊል ተሳታፊ ምልከታ ተከናውኗል፡፡ በዚህም የስርዓቶቹ አከዋወን፣ የከዋኞች ስሜት፣ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሶች ምንነት እና ገፅታ እና ማህበራዊ መስተጋብሩ ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

ሌላው አገልግሎት ላይ የዋለው ዘዴ ቃለመጠይቅ ሲሆን 8 ሴቶች እና 15 ወንዶች በአጠቃላይ 23 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስምንቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ በጋብቻ ስርዓቶቹ ውስጥ ያለፉ እና የተሳተፉ፤ ሽማግሌ(ላዛንሳ) በመሆን የጋብቻ ስርዓቶችን ያስፈፀሙ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጋብቻ ስርዓቱ በቅርብ ዓመታት ያለፉ ጥንዶችም ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ነበሩ፡፡ በዚህ ዘዴም ማህበረሰቡ ስለ ጋብቻ ስርዓቶቹ ያለውን አመለካከት ለማወቅ፣ ስለወንዶች እና ሴቶች ሚና ያላቸው ምልከታ፣ የተለያዩ ድርጊቶች፣ ቁሶች እና ቃላት ያላቸውን ማህበረሰባዊ ፍቺዎች እና ትርጓሜዎች ለማግኘት፤ እንዲሁም መረጃዎችን ለማጥራት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

በቃለመጠይቅ እና በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ለማመሳከር እና ለማጥራር ይረዳ ዘንድ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ ውይይቱም ከአምስት እስከ ሰባት ሰዎችን ባሳተፉ አራት ቡድኖችን የተካሄደ ነው፡፡ የመጀመሪያው ቡድን አምስት ወንዶችን፣ ሁለተኛው ስድስት በእድሜ ከፍ ሉ ሴቶችን፣ ሶስተኛው የፆታ ስብጥርን ያማከሉ ሰባት ሰዎችን እና አራተኛው አምስት ያገቡ ወጣት ሴቶች ተሳትፈዋል፡፡ በእነዚህ የቡድን ውይይቶችም የማህበረሰቡን የጋራ ሀሳቦች የተገኙባቸው ሲሆን በቃለመጠይቅ እና በምልከታ የተገኙ መረጃዎችም ተመሳክረውባቸዋል፡፡

ከእነዚህ ዘዴዎች በተጨማሪም የጥናቱን አካባቢ እና ማህበረሰብ ለመረዳት እና የጥናቱን ፅንሰሃሳባዊ ጉዳዮችን ለመቃኘት የሚያግዙ መረጃዎችን ከካዕላይ ምንጮች ለማግኘት የሰነድ ፍተሻ ዘዴ ተተግብሯል፡፡

### የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የጥናቱ ትኩረት የሆነው የዶርዜ ማህበረሰብ በ12 ቀበሌዎች የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ ቀበሌዎችም ዓላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ሁለት ቀበሌዎች ማለትም ሄርጶ እና አማራ ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ

ቀበሌዎች አንድ ገበያ የሚጠቀሙ ሲሆን በዋናነትም በጋብቻ ከበራዎች ውስጥ ከሚመጡ ስርዓቶች ውስጥ ያገባችን ሴት ወደ ገበያ የማውጣት ስርዓትን(የሶፌ ስርዓትን) አንድ በታ መከወናቸው የስርዓት ተቀራራቢነትን የሚያሳይ ሆኖ በመገኘቱ ሊመረጡ ችለዋል። በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ የመረጃ አቀባዮች በጋብቻ ስርዓቶች ውስጥ እንዳላቸው የተሳትፎ ልምድ፣ ፆታ እና የጋብቻ ሁኔታን መሰረት በማድረግ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል።

**የመረጃ መተንተኛ ዘዴ**

ከላይ በተገለፁ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የገላጭ እና የትርጓሜ ትንተና ስልቶችን በመከተል ተተንትነዋል። ይህም መረጃዎቹን በዝርዝር ከማቅረብ በተጨማሪ ትርጓሜን እና ፍቺዎችን ለማግኘት ወሳኝ በመሆኑ ጥቅም ላይ ውለዋል።

**ንድፈሃሳባዊ ማሀቀፍ**

የጥናቱ መረጃዎችም በማህበራዊ ሚና እና በትዕምርታዊ መስተጋብር ንድፈሃሳቦች ተቀንብበው ተተንትነዋል። የማህበራዊ ሚና ንድፈሃሳብ ዋና መሠረቱ የሥራ ክፍፍል ሲሆን በንድፈሃሳቡ አራማጆች ሃሳብ መሰረት፣ የስርዓተ-ፆታ ልዩነቶች የሚመነጩት ወንዶች እና ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲፈፅሟቸው ከሚጠበቁ ማህበራዊ ሚናዎች አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል። እነዚህ ሚናዎችም በተፈጥሮ የምናገኛቸው ሳይሆኑ በተለያዩ ማህበራዊ ሂደቶች ውስጥ የምንማራቸው እና የምናጎለብታቸው ናቸው። እነዚህ ለወንዶች እና ለሴቶች ተበልው የተመደቡ ሚናዎች ደግሞ ለእያንዳንዱ ፆታ ተገቢ ነው ተብሎ የሚታሰቡ ጠባያት፣ አመለካት እና ግንዛቤን ይፈጥራሉ(Eagly et al., 2000)። በዚህ ምክንያት የሚቀረፁ ሚናዎችም በወንዶች እና በሴቶች መካከል ለሚታየው የሚና ልዩነት ነፀብራቅ መሆኑን ይጠቅሳሉ። በመሆኑም ይህ ንድፈሃሳብ የጥናቱ ትኩረት በሆነው የጋብቻ ከበራ ውስጥ የሚመጡ ተግባራት የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ ሚና እንዴት እንደገነቡ ለማየት አይነተኛ ንድፈ ሃሳብ ሆኖ በመገኘቱ ተመርጧል። ከበራዎች በተለያዩ ትዕምርቶች የበለፁ እንደመሆናቸው፤ በእነዚህ አማካኝነት የሚገለጡ ስርዓተ-ፆታ ተኮር ትርጓሜዎችን ለማግኘት ደግሞ ትዕምርታዊ መስተጋብር ንድፈሃሳብ ግልጋሎት ላይ ውሏል። ትዕምርታዊ መስተጋብር ሰዎች እርስበርስ በሚያደርጉት ግንኙነቶች ውስጥ ትርጓሜን እንዴት እንደሚፈጥሩ የሚያሳይ ንድፈ ሃሳብ ሲሆን ሰዎች ለተለያዩ ድርጊቶች የሚኖራቸው ትርጓሜ በትዕምርቶች አማካኝነት የሚገለጥ መሆኑን የሚመለከት እሳቤ ላይ ያተኩራል (Carter and Fuller፣ 2015)። ሰዎች በሚኖራቸው መስተጋብር ውስጥ ትርጓሜን በመፍጠር ሁነቶችን ይገነዘባሉ፤ እንደየሁነቶቹ ደግሞ ተገቢነት ያለውን ጠባይ ያሳያሉ። የመስተጋብሩ አውድ ሚናን ለመከወን ቁልፍ ጉዳይ ነው።በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ይህ ንድፈሃሳብ በጋብቻ ከበራ ውስጥ የሚስተዋሉ ትዕምርቶች የሚኖራቸው ትርጓሜ የስርዓተ-ፆታ ሚናን እንዴት እንሚቀርፅ ለማየት ያግዛል።

በዚህ ጥናት ውስጥ የመረጃ አሰባሰብ እና አጠቃቀም፣ የመረጃ አቅባዮች ፍላጎት፣ ነፃነት እና ሚስጥራዊነት፣ ተጠኚ ማህበረሰብን ማክብር እና መሰል የምርምር ስነምግባራዊ መርሆችን በመከትል ተከናውኗል።

## 3. የመረጃ ትንተና

ይህ ክፍል በዋናነት ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ክፍሎችም የተጠኚውን ማህበረስብ የጋብቻ ከበራዎች አተገባበር እንዲሁም ከበራዎቹ ውስጥ ጎልተው የታዩ ስርዓት-ፆታዊ ሚናዎች ተቃኝተውባቸዋል፡፡

### 3.1. የጋብቻ ከበራ በዶርዜ ማህበረሰብ

ጋብቻ ሁለት ተቃራኒ ጥንዶች መጣመር እና መዋሃድን የሚመለከት እሳቤ መሆኑን የሚገልፅ ተለምዷዊ ብያኔ ያለ ቢሆንም አንድ ማህበረሰብ ካለው ርዕዮተዓለም አንፃር የሚቃኝ መሆኑም ይጠቀሳል (Morgan, 2007; Terian, 2004; Zonabend, 2002) ፡፡ በዶርዜ ማህበረሰብ እሳቤ መሰረት ጋብቻ በዋናነት ዘርን ከማስቀጠል አንፃር የሚቃኝ ነው፡፡ ዘርን መተካት ህይወትን እንደማስቀጠል እና ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ የመጣ ሃብትን ለማስቀጠል እንደ ዋስትና የሚታይ መሆኑ ተገልጧል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)፡፡ አንድ የማህበረሰቡ አባል ለአቅመ ጋብቻ ሲደርስ ማግባት እና መውለድ በማህበረሰቡ ዘንድ ተጠባቂ ጉዳይ ነው፡፡ ዘርን በመተካት ሂደት ውስጥ በተለይ ወንድ ልጅ መውለድ ዘርን እንደማስቀጠል ይቆጠራል፤ የአባትን ሃብት መውረስ የሚችለው ወንድ ልጅ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሴት ልጅ ስታገባ የወላጆቿን ቤት ለቃ ወደባል ጎሳ የምትቀላቀል መሆኑ እንደ ምክንያት ይታያል፡፡ በዚህም የተነሳ የቤተሰቧን ቋሚ ሃብቶች መውረስ እንደማትችል ይጠቀሳል፡፡ በመሆኑም በጋብቻ ውስጥ ሃብትን ለማውረስ እና ዘርን ለማስቀጠል ወንድ ልጅ መውለድ እንደግዴታ ይቆጠራል፡፡ ወንድ ልጅ ባልተወለደባቸው ትዳሮች አንድም ባል ሌላ ሚስት እንዲያገባ መፍቀድ አልያም የባልዬውን ታላቅ ወንድም ወንድ ልጅ፣ እንደልጅ አድርጎ መውሰድ ለሚስትዬው የሚቀርቡ አማራጮች ናቸው፡፡ በመጀመሪያው አማራጭ ከተስማማች ሁለተኛ ሚስት ያገባል በሁለተኛው ከተስማማች ደግሞ ስርዓቱን ትፈፅማለች፡፡ በዚህ ስርዓት መሰረትም የወንድሙ ልጅ በየትኛውም የእድሜ ክልል ቢሆን እንደተወለደ ህፃን ልጅ እያለቀሰ የሴትየዋን ጡት ይጠባል፡፡ እሷም ልክ ልጅ እንደወለደች ተቆጥሮ አጥብታ በስርዓት ትታረሳለች፡፡ ከዚህ ስርዓት በኋላ ልጁ የዚህ ቤት ልጅ ይሆናል፡፡ ይህም የቤተሰቡ ሃብት ተረክቦ የሚያስቀጥል ወራሽን ያስገኛል (አቶ ተሾመ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም፤ አቶ መንግስቱ፣ ዶርዜ አማራ፣ ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 2017 ዓ.ም)፡፡

በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ለጋብቻ መመስረት እንደተጨማሪ ምክንያት የሚወሰደው ረዳት ፍለጋ ነው፡፡ የወንድ ቤተሰብ ሴት ልጆች ከሌሏቸው አልያም ያሉት ካገቡ፤ ቤተሰቡን የምታግዝ ሴት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህን ፍላጎት መሰረት በማድረግም "ለእናት አባትም ጥሩ ታዛዥ ናት ጥሩ ሰራኛ ናት" ትፈለጋለች(አቶ አባይነህ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም)፡፡ ይህን በጋብቻ ውስጥ ሴቶች እንዲኖሯቸው የሚጠበቁ ጠባያትን አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም እገዛን መፈለግ ለጋብቻ መመስረት እንደሁለተኛ ምክንያት ሊታይ እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡

የዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራ በአንዴ ተከውኖ የሚጠናቀቅ ሁነት ሳይሆን፤ ሙሽሮችን በተለይ ሙሽሪትን ከሙሽራው ቤተሰብ እስከ ማህበረሰቡ ድረስ ደረጃ በደረጃ የሚቀላቅል ስርዓትን የያዘ ነው፡፡ ይህ ስርዓትም እስከ 1 ወር ከ15 ቀናት ሊወስድ ይችላል(ወ/ሮ ንግስት፣ ወ/ሮ አለሚ እና አቶ መለሰ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2017 ዓ.ም.)፡፡ ወደ ዋናው ከበራ ከመሻገር በፊት ቅድመ ጋብቻው ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ቅድመ ጋብቻ

በዚህ ክፍል የማህበረሰቡ የጋብቻ ከበራ መጀመሪያ ከሆነው የሰርግ ስርኣት ክወና አስቀድመው የሚከናወኑ እና የሚፈፀሙ ጉዳዮችን ይይዛል። እነዚህም የአጋር ምርጫ እና የሽምግልና ስርዓት ሲሆኑ የማህበረሰቡን የአጋር ምርጫ መስፈርቶች እና ደንቦች፤ እንዲሁም የሽማግሌ ሚናዎች ምን እንደሚመስሉ ያሳያል።

## የአጋር ምርጫ

የዶርዜ ማህበረሰብ የአጋር ምርጫ ጎሳን፣ ማህበራዊ መደብን፣ እድሜን፣ ስራን የመወጣት ቃትን እና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ መስፈርቶች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ጎሳ እና ማህበራዊ መደብ (social caste) አይነኬ እና መሰረታዊ መሆናቸውን ይጠቅሳል(አቶ መንግስቱ፣ ዶርዜ አማራ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)።እነዚህ ጉዳዮች አፅንዖት የተሰጠባቸው መስፈርቶች መሆናቸውን በቡድን ውይይት ወቅትም ለመገንዘብ ተችሏል። ማህበረሰቡ በተለያዩ ጎሳዎች የተዋቀረ ሲሆን የአንድ ጎሳ አባላት እንደ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ከዚህም የተነሳ የማህበረሰቡ የጋብቻ ደንብ ከጎሳ ውጭ ማግባትን የሚፈቅድ ነው። በመሆኑም፤ አንድ ሰው ማግባት ሲፈልግ የተፈላጊዋ ጎሳ ከእሱ ጎሳ ዉጭ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። የጎሳ አባልነት የሚቆጠረው በአባት የጎሳ አይነት በመሆኑ የሁለቱም ወገኖች የእናት ጎሳ ከግምት ውስጥ አይገባም። ሁለተኛው መሰረታዊ መስፈርት ማህበራዊ መደብ ነው። የዶርዜ ማህበረሰብ ልክ እንደሌሎች የጋሞ አካባቢ ማህበረሰቦች ሁሉ በሶስት ማህበራዊ መደቦች የተዋቀረ ማህበረሰብ ነው። እነዚህም ማላ፣ ማና እና ደጋላ ናቸው። ደጋላ በቆዳ መፋቅ ላይ የሚተደደሩ፤ ማና በሸክላ ስራ ላይ የሚተዳደሩ ሲሆኑ ማላ ደግሞ በሌሎች ስራዎች ላይ የሚሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው። ደጋላ እና ማናዎች በቁጥር አነስተኛ ናቸው (Freeman, 2004; Getaneh, 2004 & 2014)። በጋብቻ የአጋር ምርጫ ውስጥ ይህ መደብ በጥንቃቄ ይታያል። ማላ ከሌሎች ጋር አይጋባም፤ ደጋላና ማናዎችም የራሳቸውን አባል ነው የሚያገቡት። እነዚህ መስፈርቶች መሰረታዊ ናቸው(አቶ መንግስቱ፣ በዶርዜ አማራ፣ ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 2017 ዓ.ም፤አቶ ወልዴ እና ወ/ሮ ወርቅነሽ ፣ዶርዜ ሄርጳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም) ። ከእነዚህ በተጨማሪም፣ ለጋብቻ የምትመረጠው እንስት በቤት ውስጥ ያላት ሙያ፣ ታዛዥነት እና ስራን በአግባቡ የመወጣት ብቃት እንደ መስፈርት ይታያሉ። ሴት ልጅ ቤቷን ማስተዳደር ከመቻል፣ በእርሻ ወቅት አስታውሳ ማሳው እንዲታረስ እና በሰዓቱ እንዲዘራ ከማድረግ አንፃር ያላት ችሎታ እንደ መስፈርት ይታያል። የዶርዜ ወንዶች በአብዛኛው በሽመና ስራ የሚያሳልፉ በመሆኑ እና ለስራም ወደሌላ ቦታ ስለሚሄዱ፣ የእርሻ ሰዓት ሲደርስ አባወራውን አስታውሳ፤ ወይም ሰራተኛ ቀጥራ ማሳው በጊዜ እንዲታረስ እና እንዲዘራበት ከዛም ቀጣይ ሂደቱን የመከታተል ሃላፊነት አለባት በማለት አቶ ተክሉ ያስረዳሉ (ዶርዜ አማራ፣ ቃለመጠይቅ፣ ህዳር፣ 2017 ዓ.ም)። ከእነዚህ ሃላፊነቶች በተጨማሪ የቤት እንስሳትን የመመገብ እና የማስተካከል ስራ የሴቷ በመሆኑ፤ ይህን የማድረግ አቅም ያላት መሆኑም ከግምት ውስጥ ይገባል (አቶ አባይነህ ፣ዶርዜ ሄርጳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ህዳር ፣ 2017 ዓ.ም)። በመሆኑም በማጨት ሂደት ውስጥ፤ ከላይ የተዘረዘሩ ሃላፊነቶችን መወጣት የምትችል መሆኑ ይጣራል።

በአጠቃላይ የልጅቱ ጎሳ፣ ማህበራዊ መደብ፣ ስራ የመስራት አቅም እና ታዛዥነት ተጣርቶ ተስማሚ ሆና ከተገኘች፣ የልጁ አባት ወደልጅቱ ቤተሰብ ሽምግልና ወደመላክ ሂደት ይሻገራል። ይህ የዘር ሐረግ የማጣራት ሂደትም የቤተሰብ ዳራና የእንስቷ ሃላፊነትን የመወጣት አቅም በጋብቻ ውስጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ሂደት ውስጥ አጋርን የመምረጡ ሥልጣን በተወሰነ መልኩ የአግቢው ቢሆንም የማፅደቁ

ሃላፊነት ግን የአባት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ የአባት የሃላፊነትን እና የተሰሚነትን ደረጃም ያሳያል።

## የሽምግልና ስርዓት

በዶርዜ ማህበረሰብ የሽምግልና ስርዓት በትዳር ፈላጊው አባት የሚመራ ነው። አንድ ለጋብቻ የደረሰ ወጣት የሚፈልጋትን ሴት ከመረጠ በኋላ ለአባቱ የመናገር ግዴታ አለበት። አባትም ተፈላጊዋ ልጅ የማን ቤተሰብ እንደሆነች ካጣራ በኋላ በአካባቢው ካሉ የእድሜ ባለጠጎች ውስጥ ላዘንሳ ወይም ሽማግሌ ይመርጣል። ላዘንሳ የሚመረጠው በእድሜ ብቻ ሳይሆን ተናግሮ ማሳመን በመቻሉ፣ ባለው ተቀባይነት እና በመመላለስ ጊዜ የማይወስድ መሆኑ የሚታመንበት ሰው ነው። ላዘንሳ ምንም እንኳን ተቀዳሚ ተግባሩ ለሽምግልና ወደተመረጠችው ልጅ ቤተሰቦች ቤት ሄዶ መጠየቅ ይሁን እንጂ፤ በማህበረሰቡ የጋብቻ ስርዓት ውስጥ ተከታትለው በሚመጡ ከበራዎች ውስጥም ወሳኝ ሚናዎች አሉት(የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ የካቲት፣ 2017 ዓ.ም)።

የልጁ አባት ሽማግሌውን ከመረጠ እና ካስረዳ በኋላ ወደ ልጅቱ ቤት ሄዶ የማሳመን ሃላፊነት ይሰጠዋል። በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ሽምግልና የሚላከው በተመረጡ ቀናት ነው። እነዚህም ቅዳሜ፣ ማክሰኞ እና ሃሙስ ሲሆኑ *የሴት ቀናት* ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ቀናት ጥሩ እድል አላቸው ተብለው ስለሚታመኑ ሽማግሌ ለመላክ፣ ቤት ለመስራት እና ጋብቻ ለመመስረት ይመረጣሉ(እነ አቶ አለቴ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ የካቲት 2017 ዓ.ም.)። ይህም ማህበረሰቡ ቀናነት እና ልዝብነት የመሰሉ ጠባያትን ከሴቶች ጋር የሚያያይዝ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የልጅቱ ቤተሰብ ግለሰቡ ለምን እንደመጣ በር ላይ በሚያቆመው ሆሮርሳ (በትር) ያውቃሉ። ሆሮርሳ ጫፉ ላይ ብረት ያለው በትር ሲሆን በወንዶች ብቻ የሚያዝ ቁስ ነው። ይህ ሃገረሰባዊ ቁስ ከስልጣን እና ውሳኔ ሰጪነት ጋር ይያያዛል(አቶ ሃብታሙ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ህዳር 2017 ዓ.ም.)። ሽማግሌው የያዘውን ሆሮርሳ በር ላይ ሰክቶ ያቆማል። ይህን የተመለከቱ የቤተሰብ አባላትም ፊትለፊት የቀረበ ማንኛውም ምግብ ነክ ነገሮች ውሃንም ጨምሮ ያሸሻሉ።

በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ምግብ ወይም ውሃ መቅመስ የመዛመድ ስምምነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። በመሆኑም ሽማግሌው ጉዳዩን በአጭሩ ለመቋጨት ባገኘው እድል ሁሉ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል። በመሆኑም የልጅቱ ቤተሰቦች ይህን ለመከላከል በተቻለ አቅም ከዚያ አካባቢ ምግብና መጠጦችን ያሸሻሉ። ወደቤት ሲገባም ሰላምታ ሰጥቶ ይገባል። የልጅቷ አባት ወይም አባት ከሌለ ታላቅ ወንድ የመጡበትን ምክንያት ይጠይቃል። የመጠበትን ጉዳይ ካስረዳ በኋላ የሴቷ ቤተሰብ እኔ ቤት የደረሰች ሴት የለም ብሎ ይመልሰዋል። ይህ የመመላለስ ሂደት እስከ ሶስት ዙር ይቀጥላል። በሶስተኛው ዙርም ቤተሰቧ ለማን ልጅ ሽምግልና እንደመጣ ይጠይቃሉ።የልጁን ሁኔታ ለማጣራት እና ከቤተሰብ ጋር በመምከር ሰበብም ድጋሚ ለሶስት ዙር ሽማግሌው ይመላለሳል። በወንድ ወገን የተደረገ የጎሳ እና ማህበራዊ መደብ ማጣራት በሴት ወገንም እንደሚደረግ ተጠቅሷል(አቶ ተሾመ እና አቶ አለቴ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ጥቅምት፣ 2017 ዓ.ም)። ሶስተኛው ዙር ላይ መስማማታቸውን ይነግራሉ። በዚህ ጊዜ የሴት ቤተሰብ መስማማታቸውን ለመግለፅም ሽማሌውን ይጋብዛሉ። ከዚህ በተጨማሪም ጉዳዩን ፈፅሞ ከቤቱ ሲወጣ በባህሉ መሰረት በር ላይ ሰክቶ ያስቀመጠውን ሆሮርሳ አባት ወይም ታላቅ ወንድ ነቅሎ በክብር ይሰጠዋል። ከዚህ ቀን በፊት ይህን ድርጊት መፈፀም እንደመስማማት ስለሚቆጠር ያን አያደርጉም። ሽማግሌው የሴት ቤት መስማማታቸውን ለወንድ ቤት ሲያበስር በወንድ ቤት ግብዣ ይደረግለታል።

ከስምምነቱ ጋር ተያይዞ የልጅ ቤተሰቦች ልጁን ማየት እንፈልጋለን የሚል ጥያቄ ስለሚያቀርቡም ልጁ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

ከዚህ ስምምነት በኋላ ሽማግሌው የሰርግ ጊዜን የማስወሰን ሃላፊነት ይኖርበታል። የሰርጉን ቀን የሚወስነው የወንድ ቤተሰብ ነው። ሽማግሌውም ያን ውሳኔ ይዞ ወደ ሴት ቤተሰብ በመሄድ በተወሰነው ጊዜ እንዲዘጋጁ ይነግራቸዋል። የሰርጉ ዝግጅትም ይጀመራል። በዶርዜ ማህበረሰብ የሰርግ እለታት ማክሰኞ፣ ቅዳሜ ወይም እሁድ ናቸው።ለዚህም እንደምክንያት የሚነሳው ሰኞ እና ሃሙስ የገበያ ቀን መሆናቸው፤ እንዲሁም እሮብ እና አርብ ደግሞ የፆም ቀናት መሆናቸው እንደሆነ ተጠቅሷል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ አማራ፣ የካቲት፣ 2017 ዓ.ም)።

ከዚህ በመነሳትም፤ በዚህ ሁነት ውስጥ የወንድ ሚና በጉልህ ይታያል ማለት ይቻላል። አጋርን ከመምረጥ እስከ ስምምነት ያሉ ሂደቶች በዋናነት በወንዶች የሚፈፀሙ ናቸው። የሙሽራው አባት ቤተሰቧን የመመርመርና ላዛንሳን (ሽማግሌውን) የመምረጥ ኃላፊነት አለበት።ይህ የአባትን ሥልጣንና ተሰሚነትን በማረጋገጥ ረገድ ያለውን ሚና ያጎላል። ሌላው የወንድ ወገንን በመወከል ጉዳይ በማስፈፀሙ ሂደት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ላዛንሳ(ሽማግሌ) ነው። ይህ ሚና ለወንዶች ብቻ የተወሰነ ነው። ላዛንሳ የሚመረጠው በእድሜው፣ በማሳመን ችሎታው፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ባለው ደረጃና ታማኝነቱ ነው(አቶ አለቴ እና አቶ ተሾመ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)። በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል ዋነኛው ተደራዳሪና ተነጋጋሪ ሆኖ የሚሠራ ሲሆን ይህም ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው ቦታ ነው። ሃላፊነቱ ጥበብን፣ አንደበተ ርቱዕነትንና አክብሮትን የሚያጠይቅ እንደመሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ የተከበሩ የወንድነት ባሕርያትን ያጠቃልላል።

በወንድ ወገን በኩል በሂደቱ ውስጥ በዋናነት ከሚሳተፉት የሙሽራው አባት እና ሽማግሌው በተጨማሪ፣ የሙሽሪት አባት አልያም ታላቅ ወንድምም የውሳኔ ሰጪነት ሚና ጎልቶ ይታያል። የጋብቻ ጥያቄውን ሥርዓት በተሞላበት መንገድ የመቀበልና የመቃወም ኃላፊነት አለበት። ይህም በሙሽሪት የወደፊት ሕይወት ውሳኔ ሰጪ አካል መሆኑን ያመለክታል። በአጠቃላይ በሽምግልና ስርዓቱ ውስጥ የወንዶች ሚና ከፍተኛ ሆኖ ተሳተውሏል። በዚህ ስርዓት ውስጥ ምንም እንኳን ሙሽሪት የድርድሩ ርዕሰ ጉዳይ ብትሆንም ውሳኔ በመስጠት ረገድ ያላት ሥልጣን የተገደበ ነው።

## የሰርግ ስርዓት

የሰርግ ቀን በዋናነት ሙሽራው ሙሽሪትን የሚያመጣበት፣ የአንድነት ቃልኪዳን የሚታሰርበት እና እንደባልና ሚስት አንድ ላይ መኖር የሚጀምሩበት ቀን እንደመሆኑ፤ እነዚህ ሁነቶችን የሚያስተዋውቁና የሚያስተሳስሩ ስርኣቶች የሚከወኑበት እለት ነው። በዚህ ውስጥም ወደሙሽሪት ቤት ሄዶ ሙሽሪትን የማምጣት፣ ስጦታና ምርቃት የመቀበል ስርዓቶችን በሴቷ ቤት፤ ደም የመርገጥ፣ የጫጉላ ቤት ስርዓት እና የካጫ ስርዓት ደግሞ በወንድ ቤት የሚደረጉ ስርዓቶች ናቸው።

በሰርግ ዕለት ሙሽራው በዘመዶቹ እና ጓደኞቹ ታጅቦ በላዛንሳው ፊት መሪነት ወደ ሙሽሪት ቤት ይሔዳል። ላዛንሳው በዚህ ቀን ሆሮርሳውን ይዞ ሙሽራውን እየመራ ይወስዳል እየመራም ይመለሳል። ለሙሽሪት የሚሆኑ ስጦታዎች ደግሞ በሙሽራው እህት ታዝሎ ይወሰዳል። ላዛንሳው ሆሮርሳውን ይዞ ከፊት እየመራ ይሄዳል። የሙሽሪት ቤተሰቦች በር ላይ እንደደረሰም ሆሮርሳውን ተቀብለው ከዋናው ቤት በራፍ ላይ ተሰክቶ

ይቆማል። ይህን የሚፈፀመው የሙሽሪት አባት በወከለው ወንድ አማካኝነት ሲሆን ፈቃደኝነታቸውን ማሳያ ድርጊት ነው። ሙሽራው ወደውስጥ እንደገባም ለሙሽሪት የተወሰደው ስጦታ ይሰጣል። የሙሽሪት ቤተሰብ በስጦታው ላይ ቅሬታ ካላቸው ይቃወማሉ። ያን ተቃውሞ አለዝቦና ዋስ ሆኖ የማስተካከሉ ሃላፊነት የነገር አባቱ ይሆናል። ከቤተሰቡ ስምምነት በኋላ ሙሽሪት የመጣላትን የሙሽራ ልብስ ቀይራ ከሙሽራው ጎን ትቀመጣለች። ከዛም ምግብ እና መጠጥ ይቀርባል። በጋብቻ ስርዓቶቹ ውስጥ የሚኖሩ የምግብ እና የመጠጥ ዝግጅቶች ከእርድ ውጭ በሴቶች ይሸፈናል።

ከምግብ በኋላ የሴት ቤተሰብ ስጦታ ይሰጣል። በተለይም የአባት ቡልኮ እና የእናት ጋቢ የማይቀሩ ስጦታዎች ናቸው (ወ/ሮ ወርቅነሽ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ህዳር፣ 2017 ዓ.ም.)። ቡልኮ በማህበረሰቡ አባላት ከሚሰሩ የባህል ልብሶች መካከል ከፍተኛ ደረጃ እና ክብር የሚሰጠው ልብስ ነው። ይህን ልብስ የሙሽሪት አባት ለሙሽራ መስጠትም በአንድ በኩል የሙሽሪትን አባት ደረጃ ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ሙሽሪትን ለሙሽራው መሰተትን የሚያሳይ ትዕምርት ነው። ቡልኮ ሰጪውም ተቀባዩም ወንድ ነው። ሌሎች የሴት ወገኖችም እንደየአቅማቸው ስጦታዎችን የሚያቀርቡ ሲሆን እነዚህ ስጦታዎች በአብዛኛው ጊዜ የሙሽሪት መገልገያ የሚሆኑ እቃዎች እንደሆኑ ተጠቅሷል። የሴት ወገን ከጊዜያዊ መገልገያ እቃዎች ውጪ ለሙሽሪትም ሆነ ለሙሽራው የቋሚ ንብረት ስጦታ አይሰጥም። ከስጦታው በኋላም የምርቃት ስርዓት ተከናውኖ፤ ሙሽሮቹ እግር ስመው፤ እናትና አባት ደግሞ ምርቃቱ እንዲሰምር ምራቃቸውን ተፍተውባቸው ይሸኛሉ። ይህ ድርጊትም ምርቃታቸው እንዲሰምር እና ክፉ እንደይገጥማቸው መልካም ምኞታቸውን የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው(የተተኳሪ ቡድን ውይት፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ሚያዚያ 2017 ዓ.ም.)።

በሙሽሪት ቤት ውስጥ በሚከወኑ ሁነቶች ውስጥ በአብዛኛው የወንዶች አመራርነት በላዛንሳው፣ ሚዜዎች እና የሙሽሪት አባት ወይም ታላቅ ወንድም አማካኝነት ጎልቶ ይታያል። ላዛንሳው የወንዱን ወገን እየመራ ወደ ሴት ወገን የማድረስ፣ ከወንድ ወገን የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን የማስፈፀም፣ ሙሽሪትን ከወገኖቿ ተቀብሎ ወደ ወንድ ወገን የማምጣትን ሃላፊነት ይወጣል። የሙሽሪት አባት ለሙሽራ የሰጡትን ቡልኮ ይዞ ከፊት እየመራ ወደ ወንድ ቤተሰብ በመውሰድም ሙሽሮችን ለቤተሰብ ያደርሳል። ቡልኮውን ደግሞ ጫጉላ ቤት ወስዶ ያስቀምጣል። ይህ ድርጊትም የሙሽሪት አባት ያሳደጋት ልጁን ለወንድ ወገን ማስተላለፉን የሚያመላክት ሆኖ ታይቷል። በሰርጉ እለት በሙሽሪት ቤት ባሉ ሁነቶች ውስጥ የሴቶች ሚና ጎልቶ የሚታየው በምግብ ዝግጅትና አቅርቦት ላይ ነው። የሙሽሪት እናት በስጦታ እና ምርቃት ላይ ተሳትፎ ሲኖራት የሙሽራው እህት ደግሞ ለሙሽሪት የሄደውን ስጦታ ይዞ የመሄድና ያላትን ደግሞ ይዞ የመመለስ ድርሻ አላት። ይህም የሴቶችን የረዳትነት ተግባር የሚያሳይ መሆኑ ተስተውሏል።

በዚህ ዕለት የሚደረጉት ቀሪ ስርዓቶች በሙሽራው ቤተሰቦች ዘንድ የሚደረጉ ናቸው። ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ከቤተሰቦቹ ቤት እንደደረሰ፤ ከግቢው መግቢያ በር ላይ አባት በግ ያርዳል። ይህ ስርዓት የሚፈፀመው ሙሽራው የቤቱ ወንድ ልጆች ታላቅ ከሆነ ወይም ታላቅ ወንድሙ ቀድሞ አግብቶ ስርዓቱን የፈፀመ ከሆነ ነው። ታላቁ ካላገባ ከዚህ ስርኣት በተጨማሪ ተከታትለው የሚመጡ ስርዓቶችም አይደረጉለትም። ያመለጡትን ስርዓቶች ታላቁ ሲያገባ አብሮ ይፈፀምለታል። ሙሽሮችም የበጉን ደም ረግጠው ይገባሉ። ለፈጣሪ ምስጋና እንደማቅረብ እንደሚቆጠር ቢነገርም ዋና ዓላማው ከልጅነት ብቻ ወደባለትዳር የተሻገረው ሙሽራ የአባቱን ቅጥር፣ ባለቤትነት እና ራስነት አክብሮ እንዲኖር ቃል ማሰሪያም ሆኖ ታይቷል። ቅጥር ባለቤትነትን ያመለክታል። የቅጥሩ ባለቤት ደግሞ አባት ነው። ይህ ስርዓትም የቤቱ ራስ የሆነው አባወራ የልጁን ሽግግር መቀበያ እና እውቅና መስጫ ሆኖ ተገልጧል። በግቢው ውስጥ ከሚደረገው የምግብና

መጠጥ መስተንግዶ በኋላ ለአይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ሙሽሮች ወደጫጉላ ቤታቸው ይገባሉ። ጫጉላ ቤት ሁልጊዜ ከዋናው ቤት ኋላ የሚሰራ ሲሆን፣ ለታላቅ ልጅ በቀኝ በኩል ለታናናሾቹ ደግሞ በግራ በኩል ይሰራል። በባህሉ መሰረት የአባትን ርስት የሚወርሰው እና የአባት ተተኪ ተብሎ የሚታመነው ታላቅ ወንድ ነው። ይህም ተመራጭነትን እና ወራሽነትን ይወክላል።

በሰርግ ቀን አባት ለሙሽራው የሚሰጥን ነፃነትን ተከትሎ የሚደረገው ሁነት በኦልማ ዛፍ ተከላ ይፈፀማል። ይህን ዛፍ የሚተክለው በሰፈሩ ካሉ በእድሜ አንጋፋ ሰዎች መካከል ዘመድ ያልሆነው ተመርጦ ነው። በማህበረሰቡ ደንብ መሰረት ማንኛውም ወንድ ልጅ በአባቱ ግቢ ውስጥ ፆታዊ ግንኙነት ማድረግ በፅኑ የተከለከለ ነው። ይህ ክልከላ የሚነሳው አባት ሲፈቅድን ድንበር ሲያበጅ ብቻ ነው። ይህ ድንበር የሚበጀው ደግሞ የኦልማ ዛፍ በመትከል ነው። ይህ ዛፍ ልጅ የአባቱን ድንበር አክብሮ እንዲኖር እንደማስታወሻ የሚቀመጥ ነው። የልጅ ወደ አባወራነት መሸጋገሩ ምንም እንኳን ከአባት ደረጃ ጋር ለመስተካከል የመጀመሪያ ምዕራፍ ቢሆንም፣ ቀጥለው በሚመጡ ሁነቶች ተገፋፍቶ ደንቡን እንዳይጥስ፣ አባትን እንዳይገፋ እና እንዳይታበይ የሚያስታውስ ምልክት ሆኖ ይታያል(የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ የካቲት፣ 2017 ዓ.ም.)።

በአጠቃላይ በእነዚህ ስርዓቶች ውስጥ ወንዶች በላዛንሳው፣ የሙሽሪት አባት ወይም ታላቅ ወንድም እና በሙሽራው አባት አማካኝነት የስርዓቶቹ መሪ፣ አስፈፃሚ፣ ፈቃጅ ሆነው ሲታዩ ሴቶች ደግሞ በሁለቱም ወገን በኩል ባሉ እናቶች እና ሴት ዘመዶች አማካኝነት ምግቡን በማዘጋጀት እና በማስተናገድ ተግባር፣ በሙሽራው እህት አማካኝነት ደግሞ የአጋዥነት ተግባራት ላይ ሲሳተፉ ተስተውሏል።

**የካጫ ስርዓት**

ይህ ስርዓት ሙሽሮቹ የመጀመሪያ ተብሎ የሚታሰበውን ግንኙነት ከፈፀሙ በኋላ የሚከወን ነው። ከጫጉላ ቤት ሁነት በኋላ ሙሽራው ሱሪ ሳይለብስ የሙሽሪት አባት የሰጡትን ቡልኮ ተከናንቦ ወደትልቁ ቤት በመሄድ እናት እና አባቱን እና የቅርብ ዘመዶቹን እግራቸውን ስሞ ዘመዶቹን ደግሞ "ዮዮዮ.... "ብሎ ወደጫጉላ ቤቱ ይገባል። ይህን አከናውኖ ከተመለሰ በኋላ የካጫ ስርኣት ይከተላል። በዚህ ስርዓት ውስጥ ሙሽራው የሚለብሰው ቡልኮ ከሙሽሪት አባት የተሰጠ፣ በላዛንሳው (በሽማግሌው) አማካኝነት ጫጉላ ቤት የተቀመጠ፣ ከመጀመሪያ ግንኙነት በኋላ ደግሞ በሙሽራው የሚለበስ ልብስ ብቻ ሳይሆን የሙሽሪትን የሽግግር ሂደት የሚያሳይ ትዕምርት ሆኖ ታይቷል። አባት በእርሱ ስር የነበረችውን ልጅ ለላዛንሳው ሲያስረክብ ለወንድ ወገን አሳልፎ መስጠቱን ያመለክታል። ላዛንሳው ቡልኮውን ይዞ በጫጉላ ቤት እንዳስቀመጠ ሁሉ፣ ሙሽሪትም የሙሽራው መሆኗን፣ ከዚህ በኋላ ሙሽራው አቅራቢዋ፣ ተንከባካቢዋ እና ሃላፊዋ መሆኑን ሙሽሪትን ወደጫጉላ ቤት በማስገባት ውስጥ ያሳያል። ጫጉላ ቤት ለሙሽራው ተብሎ የሚሰራ፣ የራሱ ቤት እና ድንበር ነው። ሙሽሪት እዚህ ቤት መግባቷ ወደ ሚስትነት ለመሸጋገር የመጨረሻው ምዕራፍ መድረሷን ያሳያል። ይህ ስፍራ ሙሽሪትን ከልጅነት ሙሉ በሙሉ ወደ ሚስትነት የሚያሸጋግር፣ የሚስትነት ሚናዋን መወጣት የምትጀምርበት ወቅት ነው(አቶ መለሰ እና አቶ አርባ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ሚያዚያ፣ 2017 ዓ.ም.)።

ካጫ የመጀመሪያ ምግብ የማቅመስ ስርዓት እንደማለት ነው። ሙሽሮቹ የመጀመሪያውን ፆታዊ ግንኙነት ከፈፀሙ በኋላ የሚደረግ ስርዓት ነው። ይህም ቤተሰቡ ሙሽሮቹን እንደባልና ሚስት እንደተቀበላቸው የሚያሳይበት ሲሆን በአባት አጋፋሪነት ይከወናል። የሙሽራው አባት ለሙሽሮቹ ተብሎ በተዘጋጁ አዲስ

የምግብ ማቅረቢያ እቃዎች የቀረበውን ቅንጬ ከጫጉላ ቤቱ በር ላይ ሆኖ ለሙሽሮቹ ያቀምሳል፡፡ ከምግቡ በተጨማሪ መጠጥም ያቀምሳቸዋል፡፡ ድርጊቱንም ሶስት ሶስት ጊዜ ከባል ጀምሮ ለሚስት በማቅመስ ይፈፅማል፡፡ ሶስት የነገር ማፅኛ ሆኖ ይመጣል፡፡ ከሙሽራው ተጀምሮ ወደሙሽሪት መቀጠሉም የቤቱ ራስ ሙሽራው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሚያቀምሳቸው ሰዓትም “የልቴ አጬቴ” ብሎ ይመርቃል፡፡ ይህም ውለዱ ተባዙ እንደማለት ነው፡፡ ስርዓቱ እንደ ሙሃላ ይቆጠራል፡፡ ሙሽሮቹ ባልና ሚስት መሆናቸውን ማስተሳሰሪያ እና ማብሰሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ምርቃቱም የጋብቻው ዋናው ጉዳይ ዘር መተካት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ፤ የሚቀጥለው የቤተሰብ መገናኛ ስርዓት እስኪፈፀም ድረስ ሙሽሪት ከጫጉላ ቤት አትወጣም፤ ከእናትና አባት ጋርም አትገናኝም፡፡ ምግብ እና የሚያስፈልጓትን ነገሮች እህቶቹ፤ እህት ከሌለው ደግሞ ጎረቤት ልጅ ያደርሱላታል፡፡ሙሽሪት ጫጉላ ቤት በምትቆይበት ሰዓት በደምብ ተቀልባ አምሮባት መውጣት አለባት ተብሎ ስለሚታመን የወንድ ቤተሰብ በደንብ ይቀልቧታል፡፡ ወፍራ መውጣቷ ክብር የሚያሰጠው ለእነሱ ነው (ወ/ሮ ወርቅነሽ እና ወ/ሮ አበበች፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2017 ዓ.ም.)፡፡ እንደዚህ አይነት ሁነቶች በሌሎች ማህበረሰቦችም የተለመዱ እንደሆኑ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Dmitrieva, 2016; Gabdrakhmanova et al., 2017; Thubauville, 2012):: ይህ ስርዓት አንድም የወንድ ወገንን ደረጃ እንደማሳያ የሚታይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሙሽሪትን ዘር ለመቀበል የማዘጋጀትም ዓላማም አለው፤ መሬትን ለዘር ለማዘጋጀት የሚደረጉ እንክብካቤዎች ልብ ይሏል፡፡

በአጠቃላይ በሰርጉ ዕለት በሚፈፀሙ ስርዓቶች ውስጥ ቀድመው እንደመጡት ስርዓቶች ሁሉ ወንዶች የስርዓት መሪነት እና ጉዳይ ፈፃሚነት ሚናቸው ጎልቶ ሲታይ  ሴቶች የአገልግሎት ሰጪነት ሚናቸው ታይቷል፡፡ ስርዓቱን በመምራት መጀመሪያ ላዛንሳው፤ ቀጥሎ ደግሞ የሙሽራው አባት ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ይህም በተለይ የአባት ስልጣንን የሚያሳይ ሲሆን ያለ አባት ፈቃድ ሽግግሩ መቀጠል እንደማይችል ያመላክታል፡፡ የምግብ እና መጠጥ ዝግጅት እና የሙሽራው እህት የሙሽሪትን ስጦታዎች መያዟ በስርዓቱ ውስጥ የሴትን እንክብካቤና አገልግሎት ሚና የሚያጠናክር ሆኖ ታይቷል፡፡

### ***ጋሳ ሃፅዖ*(የቅልቅል ቀን)**

ይህ ስርዓት የቅልቅል ሁነት ሲሆን ሙሽሪትን ከሙሽራው ቤተሰብ መቀላቀሏን እነሱም እንደልጅ መቀበላቸውን የሚያረጋግጡበት ነው፡፡ ይህን ስርዓት ለማካሄድ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት ቆይታዋ የተወሰነ የአካል ለውጥ ማሳየት አለባት፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ የሚታደሙ ሰዎችን “ልጄ ቤት ገብታለች ተቀላቅላለች ደስ ብሎኛል” ብላ የምትጠራው እናት ነች (ወ/ሮ አበበች እና ወ/ሮ ወርቅነሽ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ህዳር፣ 2017 ዓ.ም.)፡፡ልክ እንደ ሰርግ ስርዓቱ ሁሉ፤ የዚህ ስርዓት ፊት መሪም ላዛንሳው ነው፡፡ በዚህ ቀን ላዛንሳው ሙሽሮቹን አስከትሎ ሙሽራው ከፊት ሙሽሪት ደግሞ ከኋላ ሆና ወደ ዋናው ቤት ይሄዳሉ፡፡ ከፊት እና ኋላ መሆን መከባበርን በዋናነት የሚያሳይ ነው፡፡ ከዋናው ቤትም ከእናት እና አባት በተጨማሪ አጎቶች እና አክስቶች ተቀምጠው ይጠብቋቸዋል፡፡ ቤቱ ከበር ጀምሮ ኮባ ይነጠፍበታል፡፡ በር ላይ እንደደረሱም የነገር አባቱ “ዎስ ዎስ” ይላል፤ ሽልሙኝ እንደማለት ነው፡፡ ቤተሰቡም እሺ በማለት ስጦታ ቃል ይገቡላቸዋል፡፡ ከዛም ከበር ጀምረው በእንብርክክ በመሄድ ከአባት በመጀመር ጉልበት ይስማሉ፡፡ ምግብ እና መጠጥ ቀርቦ ሁሉም ከተመገቡ በኋላ ሙሽሪት በይፋ ቤተሰቡን ትቀላቀላለች፡፡ ይህ ስርዓትም የሙሽሪትን የጫጉላ ቤት ቆይታ መጠናቀቅ ማሳወቂያ፤ ከቤተሰቡ ጋር መቀላቀሏን እና እነሱም እንደአንድ የቤተሰቡ አባል እንደተቀበሏት ማሳወቂያ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀን በኋላ ልጅቱ ወደትልቁ ቤት ገብታ ስራ ማገዝ ትጀምራለች፡፡

በዚህ ስርዓት ላዛንሳው አዲሶችን ተጋቢዎች በዋናነት ሙሽሪትን ከሙሽራው ቤተሰቦች ጋር የመቀላቀል ሃላፊነትን ይወጣል። የሙሽራ አባት በቀዳሚነት ለቅልቅሉ መሳካት ስጦታዎችን ቃል በመግባት ቅልቅሉን ይፈቅዳል። ሙሽሮቹ ፍቃዱን ተከትሎ ለቤተሰቡ ያላቸውን ክብር እና ታዛዥነት ለማሳየት ተንበርክከው በመሄድ ከአባት ጀምረው በመሳም ቅልቅሉን እውን ያደርጋሉ። የሙሽራው እናት ምግብ እና መጠጥ በማዘጋጀት እና በማቅረብ ድርሻዋን ትወጣለች። በዚህ ስርዓትም ወንድ የውሳኔ ሰጪነት እና የመሪነት ሚና ሲኖረው ሴት ደግሞ የመንከባከብ ሚናዋ ጎልቶ ታይቷል።

ሙሽሪት ከወንድ ቤተሰብ ጋር ከተቀላቀለች በኋላ የሙሽሪት እናት እና የሙሽራው እናት የሚገናኙበት ቀን አለ። ያን የሚያደርጉት ሙሽሪት ከማህበረሰቡ ጋር ለመቀላቀል ከሚደረገው የሶፌ ስርኣት በፊት ባለው የገበያ ቀን ሲሆን ሁነቱም “ካይሶ” ተብሎ ይጠራል፤ ሌባ እንደማለት ነው። በሚስጥር ማንም ሳይሰማ የሚገናኙበት ሁነት በመሆኑ ነው ይህ ስያሜ የተሰጠው(አቶ አራቤ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.) ።

**ቤኦ፡-ዘመድ ጥየቃ**

ሙሽሪት ከባሏ ቤተሰቦች ከተቀላቀለች በኋላ ጓደኞቿ እና ታናናሽ እህት እና ወንድሞቿ ባለችበት መጥተው የሚጠይቁበት እና እሷም ወደ ቤተሰቦቿ ሄዳ ታላላቆቿን ሰላም የምትልበት ስርዓት ነው። ይህም ከምትኖርበት ማህበረሰብ ጋር ለመቀላቀል ከምትፈፅመው የሶፌ ስርዓት ቀድሞ ይፈፀማል። በእለቱም የሙሽሪት ጓደኞች ታናሽ የሆኑ እህትና ወንድሞች ወደ እሷ በመሄድ ይጫወታሉ፣። የተዘጋጀውን ምግብ እና መጠጥም በልተው ጠጥተው ይሄዳሉ። የዚህ ስርዓት ዓላማም ሙሽሪት የተቀላቀለችው ቤተሰብ አዲስ እንደመሆኑ ወደ ነበረችበት ቤተሰብ መጥታ ለመጠየቅ እንዳትፈራ አይን መግለጫ ነው። በዚህም መሰረት፤ በነጋታው የሙሽራው ሴት ዘመዶች የሚያጠልቁላትን ዮሻ የተባለ የአንገት ጌጥ አድርጋ እና ትንሽ ልጅ አስከትላ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ለጥየቃ ትሄዳለች። እዛም ቤተሰቦቿን ብቻ ሳይሆን ጎረቤቱን ሁሉ ዙራ ትጠይቃለች። ይህንን ስርዓት ከፈፀመች በኋላም ከማህበረሰቡ ጋር የምትቀላቀልበትን የሶፌ ስርዓት ታከናውናለች።

**ሶፌ፡- ከማህበረሰብ እውቅናን የማግኛ ስርዓት**

በዶርዜ ማህበረሰብ ልማድ መሰረት አንዲት ሴት አግብታ ከላይ የቀረቡ የቅልቅል ሂደቶችን ካለፈች በኋላ በመጨረሻ የምታደርገው ስርዓት የሶፌ ስርዓት ይባላል። ይህ ስርዓት ሙሽሪትን ከማህበረሰቡ ጋር የሚቀላቅል እና ከማህበረሰቡም እንደባለትዳር እውቅና የሚያሰጣት ነው። ስርዓቱ የሚፈፀመው በገበያ ሲሆን በመስቀል በዓል ሰሞን ከሚከወነው የእርድ ቀን በፊት ባለው የገበያ ቀን ይከወናል። በእለቱም ከቤቷ ጀምረው አጅበዋት ከሚወጡ የወንድ ወገኖች በተጨማሪ የሴት ወገኖችም ገበያ በሚገኘው የመቀመጫ ስፍራ ይጠብቋታል። በዚህ ስርዓት የሚሳተፉት ሴቶች መሆናቸውም በምልከታ ተስተውሏል (ዶርዜ በዶ፣ መስከረም 12 2017 ዓ.ም).።

ሙሽሪት ወደ ገበያ ከመሄዷ በፊት የወንድ ወገን የሆኑ ያገቡ ሴቶች “ዮሻ” ተብሎ የሚጠራውን የአንገት ጌጥ ያረጉላታል። አንዲት ሴት ይህንን ጌጥ የምታደርገው ለቦኤ ቤተሰቧን ልትጠይቅ ስትሄድና ለሶፌ ብቻ ነው። ጌጡን ካደረጉላት በኋላ ቅቤ ራሷ ላይ ተቀብታ በባሏ የሴት ዘመዶች ታጅባ ወደ ገበያ ትሄዳለች። የአንገት ጌጡ ሙሽራ መሆኗንና ለሶፌ የምትወጣ መሆኗን በቀላሉ የሚያመላክት ነው። አጅበዋት ከሚሄዱት መካከልም ስርዓቱ ላይ የሚጠጣ መጠጥ በልጇ አክስቶች አማካኝነት ይወሰዳል። ገበያ እንደደረሱ

በአጃቢዎቿ ተከበ ገበያውን ትዞራለች። ዙራ ስትመጣም ተቀምጠው ከሚጠብቋት ዘመዶቿ ጋር ተቀላቅለው በኮባ ላይ ትቀመጣለች። ሙሽራዋ የተቀበችው ቅቤም ከራሷ ላይ ይነሳና በትንሹ ያጀቧት ሴቶች ይቀባሉ። በዚህ እለት የሙሽራው ሴት ዘመዶች እና የሚስት ሴት ዘመዶች ይቀላቀላሉ። የሁለቱ ወገኖች ከተቀላቀሉ በኋላ በወንድ ቤተሰብ ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን "ማዳ" ተብሎ የሚታወቅን መጠጥ ለሁለት ለሁለት በመዳበል ይጠጣሉ። ይህን መጠጥ የሴት ወገን የሆኑ ሴቶች በሙሉ ይጠጣሉ። ስርዓቱ ላይ ባይታደሙ እንኳን በእናታቸው አልያም በእህታቸው ተቆጥሮ ይወሰዳል(ወ/ሮ መነን፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ አማራ፣ ህዳር፣ 2017 ዓ.ም.)። የሙሽሪት ባል ከጓደኞቹ ጋር በመሆን መጠጡ በሚጠጣት ሰዓት በሩጫ በመምጣት "ዮዮዮ…" ብለው ሰላማታ በመስጠት በፍጥነት ይሄዳሉ።

ስርዓቱ በእናቶች ምርቃት ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። ሙሽሪት አድርጋ የሄደችውን ዮሻ ባለቤቶቹ መጥተው ሲወስዱም፤ በምትኩ እሷን ቅቤ መቀባት አለባቸው። ከዚህ ቀን በኋላ በቀጣይ በሚመጡ ገበያዎች ላይ ከዘመዶቿ ጋር ባህላዊ መጠጥ (ማዳ) ይጠጣሉ። ይህ መጠጥ ከገብስ የሚሰራ የአልኮል ይዘቱ በጣም አነስተኛ መጠጥ ሲሆን ከማር ጋር በመቀላቀል እንደሚዘጋጅ ወ/ሮ አበበች ገልፀዋል(ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.) በእነዚህ ገበያዎች የሚጠጣውን መጠጥ የሚያመጡ በሰፌው ላይ ተገኝተው የጠጡ የሴት ወገኖች ናቸው። በአጠቃላይ ይህ ስርዓት ሙሽሪትን ከማህበረሰቡ ጋር የሚቀላቅል በመሆኑ፤ ከዚህ ቀን በኋላ በማንኛውም ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ እና ገበያ የመውጣት ፍቃድን የሚጎናፅፋት ነው። እንደ ሙሉ ባለትዳርም የምትቆጠርበት እና ሌሎች ባለትዳር ሴቶች የሚያከናውኗቸውን ጉዳዮች ማከናወን የሚያስችል መብት የምታገኝበት እለት ነው። ስርዓቱ ሙሽሪትን ከማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀል ወደፊት የሚጠብቃትን ማህበራዊ ተሳትፎ እና ሚና ማስጀመሪያ ነው።

በዚህ ስርዓት ውስጥ የሚታዩት ለጋ ቅቤ፣ "ዮሻ"፣ ኮባ እና መጠጥ በዋናነት ለመውለድ ከመዘጋጀት እና ዘርን ከማብዛት ጋር የሚያያዙ ትዕምርቶች ሆነው ሲታዩ በስርኣቱ መጨረሻ ላይ የሚከወነው ምርቃት እንዲሁም ሰፌ ስትወጣ እና ከባሏ ዘመዶች የተዋሰችውን "ዮሻ" ስትመልስ ባለው የቅቤ መቀባት ሂደት ያለው ምርቃት፤ ጋብቻን ዘር ከመተካት፣ ሙሽሪትን ደግሞ ዘርን ለመቀበል ከማዘጋጀት ጋር የሚያያዝ ሆኖ ታይቷል። ስርዓቱ ሙሽሪትን ከማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀል ወደፊት የሚጠብቃትን ማህበራዊ ተሳትፎ እና ሚና ማስጀመሪያ ነው። ይህም ስርዓቱ በሚከወንበት የቦታ ምርጫ ይታያል። ገበያ የተለያየ የማህበረሰብ ክፍል የሚገኝበት፤ የህዝብ ሃብት ነው። ሴቶች ብቻ የሚሳተፉባቸው የሰፌ እና የእናቶች መገናኛ ሁነቶች የሚከወኑትም በዶርዜ ቦዶ የገበያ ቦታ ነው።

## በሎሶ ፓሻ፡- የአማች ስጦታ

በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራዎች ውስጥ የመጨረሻው ስርዓት በሎሶ ፓሻ ሲሆን ሙሽራው ለአማቶቹ የስጋ ስጦታ የሚወስድበት ቀን ነው። ይህ ስጦታ የሚወሰደው የመስቀል እርድ እለት ነው። ሙሽራው ለሰርጉ ቀን ከአባት ቡልኮ ከእናት ደግሞ ጋቢ መውሰዱን ታሳቢ በማድረግ የሚወሰድ ሲሆን ለአባት "ዘኮ በጋ" በመባል የሚታወቅ የስጋ አይነት ለእናት ደግሞ "ሉኩሞ" ተብሎ የሚታወቅ የስጋ አይነት ይወሰዳል። ለአባት የሚወሰደው የስጋ አይነት በመጠን ተለቅ ያለ ሲሆን በሙሽራው እህት ተሸካሚነት ሰው እንዲያየው ተደርጎ ይወሰዳል። ለእናት የሚወሰደው ስጋ ደግሞ በሙሽራው ሚዜ ወደታች ተሸፍኖ እና ደበቅ ተደርጎ ይያዛል።

እነዚህን ስጦታዎችን ይዞ ሲሄድ በሙሽሪት ቤተሰቦች የተዘጋጀውን ምግብ ቀምሶ ይወጣል። ከዚህ ቀን በኋላም እንደ ቤተሰቡ አቅም ለተከታታይ ቀናት እየተጠሩ ይጋበዛሉ። ይህን ስርዓት ሙሽራው ከፈፀመ በኋላ ከቤተሰቡ ጋር እንደተቀላቀለ ስለሚቆጠር በማንኛውም ቤተሰባዊ ጉዳይ ላይ መሳተፍ የሚያስችለውን ሙብት ያገኛል(አቶ አለማየሁ፣ የተተኳሪ ቡድን ውት፣ ዶርዜ አማራ፣ ታህሳስ 2017 ዓ.ም.)።

ይህ ስርዓት ሙሽራው ለሙሽሪት ቤተሰቦች ያለውን ክብር ቁርጠኝነት የሚያሳይበት እንደሆነ ቢታመንም ከዚህ የዘለለም መልዕክት አለው። ለአባት የሚወሰደውን ስጋ ተሸክማ መውሰድ የእህት ድርሻ መሆኑና ማህበረሰቡ እያየው መሄዱ፤ ለቤተሰቡ ከሚሰጠው ክብር እና አቅራቢነትን ከመግለፁም በላይ ዘር የማስቀጠልን ሃሳብ የሚያነሳ መሆኑ ተስተውሏል። ስጋ በአብዛኛው ጊዜ ከጥንካሬን እና ከድፍረት ጋር የሚያያዝ አንድምታ ያለው ትዕምርት እንደመሆኑ ከወንድነት ጋር ተያይዞ እንደሚነሳ የተለያዩ አጥኚዎች ያመላክታሉ (Adams, 2010; Bourdieu, 2013; Jansen, 1997; Ruby & Heine, 2011; Sobal, 2005)። በዶርዜ ማህበረሰብም በተመሳሳይ መልኩ ታይቷል።

## 3.2. በጋብቻ ከበራዎች ውስጥ የስርዓተ-ፆታዊ ሚና አገነባብ ትንተና

ይህ ክፍል ከላይ በቀረቡ የጋብቻ ከበራዎች ውስጥ በታዩ የተለያዩ ድርጊታዊ፣ ቃላዊ እና ቁሳዊ ገፅታዎች ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች እንዴት እንደተቀረፁ የሚታይበት ሲሆን፣ በከበራዎቹ ውስጥ ጎልተው በታዩት ጉዳዮች ማለትም ዘር መተካት፣ ውሳኔ መስጠት፣ ታዛዥነት እና አክባሪነት እንዲሁም ተንከባካቢነት በሚሉ ይዘቶች አማካኝነት እንደሚከተለው ይተነተናሉ።

### ዘር መተካት

በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ እሳቤም ሆነ ከበራዎች ውስጥ ጎልቶ ከሚመጡ ጉዳዮች ውስጥ ዋናው ዘር መተካት ወይም መውለድ ነው። ይህን ጉዳይ የሚያመላክቱም የተለያዩ ገፅታዎች ሲኖሩ በሂደቱም የወንድን እና የሴትን ሚና በተለያየ መልክ ያሳያሉ።

ዘር በመተካት ሂደት ውስጥ የወንድን ሚና ከማሳየት አንፃር በከበራዎች ውስጥ ከተስተዋሉ ሁነቶች አንዱ ስጦታ ነው። በጋብቻ ከበራዎች ውስጥ በሰርጉ እለትም ሆነ በቅልቅል ቀን፤ የሙሽራው አባት ለሙሽራ ከሚሰጠው ስጦታዎች ውስጥ ዋናው መሬት ነው። ይህ የሚሆነው ለሙሽራ ብቻ ነው። በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ሴቶች  አግብተው የሚሄዱት ወደሌላ ጎሳ በመሆኑ የመሬት ስጦታና ውርስ አያገኙም፤ ሃብቱ ወደዛኛው ጎሳ እንዳይሄድ የመከላከያ መንገድ መሆኑ ተስተውሏል። ሴት ልጅ ብቻ በተወለደባቸው ትዳሮች ውስጥ ወንድ ልጅ ለማግኘት ሁለት አማራጮች አሉ። የመጀመሪያው አባወራው ሌላ አግብቶ ወንድ ልጅ ለማግኘት መሞከር ሲሆን፤ ይህ ካልተሳካ የወንድሙን ወንድ ልጅ በጉዲፈቻ መቀበል የተለመደ እንደሆነ አቶ ተሾመ አብራርተዋል(ቃለ መጠይቅ፣ ዶርዜ ሄርጶ፣ ታህሳስ 2027 ዓ.ም.)። መሬት የግለሰብ ሃብት ብቻ ሳይሆን የጎሳም ጭምር መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም ይህንን ስጦታ ለማግኘት ወንድ መሆን፤ ያገኙትን ሃብት ለማስተላለፍ ደግሞ ወንድ መውለድ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ከዚህ ተጨማሪም፣ በፆታዊ የስራ ክፍፍሉ ውስጥ የሚታዩት የመቆፈር፣ የመትከል እና የመዝራት የስራ ድርሻዎችም የወንዶችን ዘር ሰጪነት እና ዘር አስቀጣይነት ሚና በትይዩ የሚያሳዩ ሆነው ታይተዋል።

በጋብቻ ስርዓተ ከበራዎች ውስጥ አገልግሎት ላይ ከሚውሉ ቁሶች ውስጥ ለጋ ቅቤ፣ ከባ እንዲሁም ምርቃት እና የመሸከም ሚናዎች፤ ዘር በማስቀጠል ሂደት ውስጥ የሴትን ቦታ እና ሚና የሚያሳዩ ትዕምርቶች ሆነው

ተስተውለዋል። ለጋ ቅቤ በተደጋጋሚ ስርዓቶች ላይ ለሴቶች ብቻ የሚቀባ ሲሆን በዋናነት ሶፌ ስትወጣ እና ከባሏ ዘመዶች የተዋሰችውን "ዮሻ" ስትመልስ ሴቶች ሲቀቡ ተመላክቷል። ቅቤው ከሙሽሪት ራስ ላይ ሲቀባ ውለጂ እርጥብ ያርግሽ ከሚል ምርቃት ጋር ነው። ቅቤ በባህሪው ልል የሆነ፣ በቀላሉ ወደፈሳሽነት የሚቀየር እንደመሆኑ በቀላሉ የማረስረስ ባህርይ አለው። የአዘገጃጀት ሂደቱም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በሴቶች የሚከወን ነው። ምንጩ ወተት መሆኑ ደግሞ ከእናትነት ጋር ያዛምደዋል። በስርዓቶቹ ውስጥ ተደጋግመው ከሚመጡ ቁሶች መካከል ኮባ ሌላው ነው። ኮባ በቤተሰብ መቀላቀያ ቀን ከባሏ ጋር ተንበርክካ የምትሄድበት፣ በሶፌ ስርዓት ደግሞ የምትቀመጥበት ቁስ ሆኖ ታይቷል። ኮባ የእንሰት ቅጠል ነው። እንሰት በየትኛውም የዶርዜ ማህበረሰብ ጓሮ የማይጠፋ፤ ለቤት የምግብ ፍጆታ የሚያገለግል፣ ዓመቱን ሙሉ እርጥብነቱን የማያጣ፣ እንዲሁን ተቆርጦ በቶሎ የማይደርቅ የተክል አይነት ነው።

በእነዚህ ገፅታዎች ውስጥ እርጥብነት ጎልቶ የሚታይ ሃሳብ ነው። እርጥብነት ለምለምነትን የሚያመላክት ሲሆን ይህም ዘር ለመቀበል መዘጋጀትን፣ ዘርን ተቀብሎም ፍሬ መስጠትን የሚያስከትል ሁነት ነው። ይህ ለዘር የመዘጋጀት ሃሳብም ከላይ ከተጠቀሱ ማሳያዎች በተጨማሪም ሙሽሪት በጫጉላ ቤት በሚኖራት ቆይታ ውስጥም በሰፊው ይስተዋላል። የጫጉላ ቤት ስርዓት እንደማስጀመሪያ የሚታየው ሙሽራው የሙሽሪትን ክብረ ንፅህና በመውሰድ ነው። ከዚህ ሁነት በኋላ ነው አባት እንደባልና ሚስት መሆናቸውን የማስጀመሪያ ምግብ የሚያቀምሳቸው። ሙሽሪት የሰውነት ለውጥ እስከምታሳይ በሰፊው እና በአግባቡ ትቀለባለች፤ እንክብካቤ ይደረግላታል። ይህም እንክብካቤ ምንም እንኳን ለሙሽሪት ቤተሰቦች ልጃቸውን በአግባቡ መያዛቸውን ማሳያ ነው ተብሎ ቢታሰብም ሙሽሪትን ዘር ለመቀበል የማዘጋጀትም ዓላማም አለው፤ መሬትን ለዘር ለማዘጋጀት የሚደረጉ እንክብካቤዎች ልብ ይሏል።

ሌላው በከበራዎቹ ውስጥ የሴት ሚናን አመላካች ከሆኑ ገፅታዎች መካከል መሸከም አንዱ ነው። በጋብቻ ከበራ ውስጥ የሙሽራ እህት የሙሽራን ወገን ወክላ የመሸከም ሃላፊነት ይሰጣታል፤ የጥሎሽ አልባሳትን ወደ ሙሽሪት ቤት የመውሰድ፣ የሙሽሪት እቃዎች ወደ ሙሽራው ቤት የማምጣት፣ ለአባት የሚሰጠውን የስጋ ስጦታ እንዲሁም ለሶፌ ስርዓት የሚያገለግል መጠጦችን ወደ ገበያ የማድረስ ሃላፊነት አለባት/አለባቸው። ይህን ሃላፊነት የሚወስዱት እህቶቹ፤ ከሌለው ደግሞ አክስቶቹ አልያም ሴት ዘመዶቹ ናቸው። በእነዚህ ሁነቶች ተደጋግሞ የሚመጣው የመሸከም ጉዳይ በፆታዊ ስራ ክፍፍል ልማድም በሰፊው የሚስተዋል ነው፤ መሸከም በአብዛኛው የስራ ዘርፍ ውስጥ የሴት ድርሻ ነው። በእርሻ ስራ ውስጥ ማዳበሪያን(ፍግን) ተሸክሞ ወደ እርሻ ቦታ መውሰድ እና የተሰበሰበ እህልን ወደቤት ማምጣት የሴቶች ስራ ብቻ ነው። ይህም ከተፈጥሯዊ የሴት ልጅ ሚና ጋር በእጅጉ ይዛመዳል። መሸከም እርግዝና አመላካች ነው፤ ዘርን መሸከም የደረሰ ፍሬን (ልጅንም) አዝሎ ማሳደግ የሴት ልጅ ሃላፊነት ነው። ከዚህ በመነሳትም፤ በተደጋጋሚ የሚመጡት የመሸከም ድርጊቶች ከስራነት በዘለለ ሴት ልጅ በተፈጥሮ ከተሰጣት አርግዞ የመውለድ እና ልጅ የማሳደግ ሚና ጋር የተያዘዘ ነው። በመሆኑም፤ ዘር በመተካት ሂደት ውስጥ ሴት ዘርን ተቀብሎ ለፍሬ የማድረስ ሚና እንዳላት በእነዚህ ገፅታዎች ውስጥ ተስተውሏል።

በአጠቃላይ ዘር በማስቀጠል ሂደት ውስጥ ወንድ የዘሩ ባለቤት፤ ሴት ደግሞ ዘሩ ፍሬ አፍርቶ ራሱን እስኪችል ድረስ ተንከባካቢ ሆነው እናገኛለን። ይህም ከማህበረሰቡ የስርዓት-ፆታ ሚናዎች እሳቤ በመነሳት፤ ወንድ የባለቤትነት፣ ሴት ደግሞ የአገልግሎት ሰጪነት ድርሻ እንዳላቸው ያመላክታል።

**ውሳኔ ሰጭነት**

በዶርዜ ማህበረሰብ የቤተሰብ መዋቅር ውስጥ የቤት ራስ ተብሎ የሚታመነው አባወራ ነው፡- መሬት፣ ቤት እና ልጆች የእርሱ ናቸውና። ይህም አባወራውን ቤቱን እና ንብረቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣንን ያጎናፅፈዋል። ይህ የውሳኔ ሰጭነት ሚናም በማህበረሰቡ የጋብቻ ከበራዎች ውስጥ ባሉ ሁነቶች ውስጥ ተስተውሏል።

በጋብቻ ከበራዎች ውስጥ ከአጋር መረጣ እስከ ቤተሰብ ቅልቅል ድረስ ባሉ ሂደቶች ውሳኔ ሰጪነት እና መሪነት በዋናነት የወንዶች ሚና ሆኖ በሰፊው ታይቷል። በዚህ ውስጥም የሙሽራ አባት፣ ላዛንሳ እና የሙሽሪት አባት በውሳኔዎች ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸው አካላት ናቸው። አንድ ለማግባት ያሰበ ወጣት የመረጣትን ልጅ ለአባቱ ከነገረበት ሰዓት ጀምሮ ባሉ ሂደቶች ውስጥ በዋናነት ላዛንሳው የሚሳተፍ ሲሆን ወሳኞቹ ደግሞ የተጋቢዎቹ አባቶች ናቸው። በዚህ የሽምግልና ሂደት ውስጥ የሙሽሪት አባት ድርሻ ለጋብቻ መፍቀድ ሲሆን በተለይ የወንድ አባት ከጋብቻ የተመረጠችውን አጋር የማፅደቅ፣ የነገር አባትን መርጦ የመላክ፣ የሰርግ ቀንን የመወሰን፣ የሙሽሮቹን ጥምረት በካጫ ስርዓት የማፅደቅ፣ መተዳደሪያቸውን በስጦታ መልክ የመስጠት፣ እና በጋሳ ሃፅያ ስርዓት ሙሽሪትን ከቤተሰብ ጋር የመቀላቀል ውሳኔዎችን የማሳለፍ ሃላፊነት አለው።

ከበራዎች የሚከወኑበት ቦታ ሌላው ከውሳኔ ሰጭነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እሳቤዎች የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል። በተለይ በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ በቤተሰቡ ግቢ እና ቤት ውስጥ የሚከወኑ ሁነቶች በሙሉ በአባት ፈቃጅነት እና ውሳኔ ሰጪነት ላይ የሚመሰረቱ ናቸው። የሰርጉ ቀን ያሉ ክዋኔዎች በላዛንሳው መሪነትና በአባቶች ወሳኝነት ይከወናሉ። ይህም በባህሉ መሰረት የቤት ባለቤት አባወራው እንደመሆኑ፤ በቤቱ ዙሪያ ለሚከወኑ ማናቸውም ክስተቶች ውሳኔ እና እውቅና የመስጠቱን ሃላፊነት የራሱ እንደሆኑ ያሳያል። በዶርዜ ማህረሰብ መሬት እና ቤት የወንዶች ነው ተብሎ የሚታመን መሆኑን በሌሎች ጥናቶችም ተጠቁሟል((Olmstead, 1975; Getaneh, 2004 & 2014)።

ሌላው የጋብቻ ከበራዎች ከሚከወኑባቸው ቦታዎች ውስጥ በገበያ ቦታ የሚከወኑ ከበራዎች ከሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ሚና አንፃር ይተሳሰራሉ። ሴቶች ብቻ በሚያሳትፉባቸው የእናቶች መገናኛ እና የሰፌ ስርዓቶች ውስጥ የመውጫ ጊዜን የመወሰን ሃላፊነት የእናቶች ነው። ይህም ሴቶች የሚወስኑት ሴቶችን ብቻ በሚያሳትፉ ስርዓቶች ውስጥ ሲሆን ሁለቱንም ፆታዎች በሚያሳትፉ ጉዳዮች ደግሞ ወንዶች ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት እንዳላቸው ያመለክታል።ገበያ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ሰዎች በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፉበት እና ማህበራዊ ሁነቶች የሚከወኑበት የማህበረሰብ ሃብት የሆነ ስፍራ ነው። ሴቶች እዚህ ቦታ ላይ መከወናቸውም፤ በሁለቱም የማህበራዊ ደረጃ ለውጦቻቸው እንደ ማህበራዊ ሽግግር ስለሚቆጠሩ፣ ሽግግሩን ለማጽናት ማህበራዊ እውቅና የሚያስፈልጋቸው መሆኑን አመላካች ነው።

በአጠቃላይ በዶርዜ ማህበረሰብ ባህል መሰረት ወንድ የቤቱ እና የመሬት ባለቤት እንደመሆኑ አብዛኛው የውሳኔ ሰጭነት ሚና አለው። ሴቶች ራሳቸው ብቻ የሚሳተፉባቸው ሁነቶች ውስጥ ውሳኔ የሚሰጡ ሲሆን ሁነቶቹም በማህበረሰቡ እይታ ውስጥ ይከወናሉ።

**ታዛዥነት እና አክብሮት**

በዶርዜ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ጎልተው ከሚታዩ እሴቶች ውስጥ ታላቅን ማክበር አንዱ ነው። በጋብቻ ከበራዎች ውስጥ በሚመጡ በርካታ ሁነቶች ውስጥም ይህ ተስተውሏል። በሰርጉ እለት የሚደረገው ደም

የመርገጥ ስርዓት እና የኦልማ ዛፍ ተከላ፣ የጫጉላ ቤት አቀማመጥ፣ በጫጉላ ቤት መቆየት እና በቅልቅል ቀን ተንበርክኮ የመሄድ ሁነት፤ ቤተሰብን በዋናነት አባትን የማክበር እና የመታዘዝ አመላካቾች ሆነው ታይተዋል። የሰርግ ቀን ሙሽሮች የሚያከናውኑት በአባት ወይም አባት ከሌለ በታላቅ ወንድም የሚቀርብን የበግ ደም የመርገጥ ስርዓት ከምስጋና ማቅረቢያነት በዘለለ ሙሽሮቹ የአባትን ቅጥር አክብረው እንዲኖሩ ቃል የማሰሪያ ስርዓት ነው። ሌላው ከማክበር ጋር ተያይዞ አመላካች የሆነው የኦልማ ዛፍ ተከላ ነው። ይህ ዛፍ ልጅ የአባቱን ፈቃድ አክብሮ በተፈቀደለት ቦታ ብቻ እንዲኖር እንደማስታወሻ የሚቀመጥ ነው።

በጋብቻ ስርዓቶች ውስጥ ሌላው ቦታን አውቆ፤ አባትን አክብሮ መኖርን ከሚያሳዩ ሁነቶች አንዱ የጫጉላ ቤት አቀማመጥ ነው። የጫጉላ ቤት ምንጊዜም የሚሰራው ከዋናው ቤት በስተጀርባ ነው።ይህም ልጅነትን፣ ታናሽነትን እና ተከታይነትን የሚያሳይ ነው። በጋብቻ ባህሉ ከአባት በተጨማሪ አባትን የሚተካ ተብሎ የሚታሰብን ታላቅ ወንድምን ማክበርም በጋብቻ ባህሉ ደንቦች ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ታላቅ ሳያገባ ታናሽ ቀድሞ ካገባ አብዛኞቹ ከበራዎች አይደረጉለትም፡- በግ አይታረድም፣ የካጫ ስርዓት አይኖርም ሶፌም አይታሰብም። ለታላቅ ቀድመው መደረግ ያለባቸውን ክዋኔዎች ለታናሽ አይደረጉም። ታናሽ ይህን ክብር የሚያገኘው ታላቅ ሲያገባ ነው። ከሙሽራው በተጨማሪም ሙሽሪት ታላቋ ሳታገባ ቀድማ ካገባች የሶፌ ስርዓት መፈፀም አትችልም። ልክ እንደ ወንዱ ሁሉ ታላቋ አግብታ ሶፍ ስትወጣ አብራ ትወጣለች።

በቅልቅል ቀን የሚከወኑት በጉልበት መሄድ እና ማጎንበስ ታናሽነትን በማሳየት ለቤተሰብ ያለ ክብርን እና ለትዕዛዝ ዝግጁ መሆንን የሚያመለክት ነው። ሙሽሪት የጫጉላ ጊዜዋ ማለቁን በሚታወጅበት በዚህ ቀን በይፋ ቤተሰቡን ትቀላቀላለች፤ የዋናውን ቤት ስራ መስራት የምትጀምርበት እና ከባል እናት ጋር በጋራ ለመስራት እንደ ቃል ኪዳን የሚታይ ቀን ነው። በስርዓቱ ውስጥ ከኋላ መሆን ሌላው ከማክበር ጋር የተያያዘ ሁነት ነው። በጋብቻ ባህሉ ውስጥ በርካታ ቦታዎች ላይ ይህን እንገኛለን። በሰርጉ ቀን የነገር አባትን ማስቀደም፣ የጫጉላ ቤት የሚሰራበት ቦታ እና ወንድን ማስቀደም (ሲገባ፣ ሲጎረስ፣ ሲጠጣ) ተጠቃሾች ናቸው። በነዚህ ሁነቶች ውስጥ ሌላን ማስቀደም ከክብር ጋር የተያያዘ ነው፤ አባትን እና ባል ከማክበር ጋር። ከዚህ በተጨማሪም ሙሽራው ለሙሽሪት ቤተሰቦች በሚወስደው የስጋ ስጦታም ለሚስቱ ወገኖች ያለውን ክብር የሚያሳይበት ነው። ሴቶች ብቻ በሚሳተፉባቸው ከበራዎችም ታላቆችን ማስቀደም የተለመደ ነው። በመሆኑም በማህበረሰቡ ባህል ታላቅ ተብለው የሚታሰቡ አካላትን ማክበር በእነዚህ ከበራዎች ውስጥም ተስተውሏል። በተለይም ሚስት ለባሏ ቤተሰቦች እና ለባሏ ታዛዥ መሆን፣ ማክበር እና ማገዝ የሚጠበቁባት ባህርያት መሆኑን በእነዚህ ሁነቶች ማየት ይቻላል።

## መንከባከብ

በዶርዜ ማህበረሰብ የስራ ክፍፍል መሰረት ቤትን ማለትም የቤተሰብ አባላትን፣ እንስሳትን እና ጓሮን በአጠቃላይ የመንከባከብ ሃላፊነት የሴቶች ነው። ይህ የሴቶች መሰረታዊ ድርሻ ተደርጎ ይወሰዳል። በጋብቻ ከበራዎች ውስጥም ይህ የሴቶች ሚና በሁለት መልኩ ይታያል፡- በአንድ በኩል ሰጪ በሌላ በኩል ደግሞ ተቀባይ ሆነው። ወንዶች በዚህ ገፅታ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ተቀባይ ሆነው ይታያሉ። በከበራዎች ውስጥ ባሉ ዝግጅቶች የምግብ ዝግጅቶች ሙሉ በሙሉ በሴቶች የሚከወኑ ናቸው።

በሌላ በኩል በእነዚህ ከበራዎች ውስጥ ሴቶች(ሙሽሪት) እንክብካቤን የሚያገኙባቸው ሁኔታዎች አሉ። የጫጉላ ቤት ቆይታ እና ስጦታ ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው። በጫጉላ ቤት ቆይታ ሙሽሪት ምንም ሳትሰራ ሰውነቷን ይገነባሉ ተብለው የሚታሰቡ ምግቦች ትመገባለች። በሰርጓ ወቅትና ከዛ በኋላ በሚመጡ ሁነቶች

ውስጥም የተለያ ስጦታዎች ይቀርቡላታል። እነዚህ ስጦታዎች በአብዛኛው አልባሳት ናቸው። አልባሳት በአብዛኛው ጊዜ ራስን ከማስዋብ አንፃር የሚታዩ ናቸው። እነዚህን እንክብካቤዎች የምታገኘው ለተወሰኑ ጊዜያት ብቻ ሲሆን ቀናቱ ሲያልፉ ወደ መደበኛ ህይወቷ ትመለሳለች። በአጠቃላይ በጫጉላ ቤት የሚደረጉ እንክብካቤዎች እና እስከ ሶፌ ድረስ ያሉ ሁነቶች ላይ የሚከወኑ ሙሽሪትን በምግብ እና በቅቤ የመንከባከብ፣ በዮሻ የማስጌጥ እና ኮባ ላይ የማስሄድ እንዲሁም የማስቀመጥ ክዋኔዎች፤ ሙሽሪት በተቻለ መጠን በፍጥነት ዘር ማስቀረት እንድትችል እና ለቤተሰቡ ልጅ እንድትሰጥ ለማስቻል የሚደረጉ እንደሆነ ተስተውሏል።

## 4. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

የጋብቻ ከበራዎች የተጋቢዎችን ማህበራዊ ደረጃ እና ሚና መሻገርን ተከትለው የሚመጡ እንደመሆናቸው ከሚሻገሩበት ደረጃ ጋር የተያያዙ ሚናዎችን የሚያስተዋውቁ ናቸው። የዚህ ጥናት የመጀመሪያ ንዑስ ዓላማ በጋብቻ ሥነ-ስርዓቱ ውስጥ የሴቶችን እና የወንዶችን ተግባራት መለየት ነው። በጥናቱ ትንተና ክፍል እንደተብራራው፣ በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ስርዓቶች ውስጥ ወንዶች በሚሳተፉባቸው ስርዓቶች ውስጥ ስርዓት ከመምራት እና ከማስፈፀም ጋር በተያዙ ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል። በእነዚህ ስርዓቶች ውስጥ ሴቶች የምግብ እና ተያያዥ የዉስጥ ጉዳዮችን በመፈፀም እና ከአጋዥነት ሚና ጋር በተያያዙ ተግባራት ላይ መሳተፋቸው ተገልጧል። በዚህም መሰረት የማህበረሰቡ ልማዳዊ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ወንድነትን ተግባራትን ከመፈፀም እና ከመምራት ሚናዎች ጋር ሴትን ደግሞ ከተንከባካቢነት ሚናዎች ጋር የሚያያዝ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ጥናት በተከተለው የማህበራዊ ሚና ንድፈሃሳብ እሳቤ መሰረት ልማዳዊ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ወንድን ከአቅራቢነት ሴትን ከተንከባካቢነት ሚና ጋር የሚያያይዝ እና ይህም ከማህበረሰቡ የፆታ ስራ ክፍፍል የሚነሳ መሆኑን ያነሳል (Eagly et al, 2000; Thobejane & Khoza, 2014)። በተመሳሳ መልኩ በዚህ ጥናት ግኝት መሰረትም፣ በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራዎች ውስጥ በሚገኘው ፆታን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ወንድነትን መሪነት እና አቅራቢነት ሴትነትን ደግሞ ከተንከባካቢነት ሚናዎች ጋር የሚያዛምድ መሆኑ በጥናቱ ታይቷል።

ሌላው የጥናቱ ዓላማ በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ የሚከወኑ ልማዶች እና ትዕምርቶች ለስርዓተ-ፆታ አገነባብ ያላቸውን አንድምታ ማብራራት ነው። የዶርዜ ማህበረሰብ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ጋብቻ ከበራዎች ውስጥ ጎልተው በታዩ ቃላዊ፣ ድርጊታዊ እና ቁሳዊ ገፅታዎች ውስጥ ዘር ከመተካት፣ ውሳኔ ከመስጠት፣ ከመንከባከብ፣ ከታዛዥነት እና ከማክበር ጋር የተያያዙ ሃሳቦች ቀርበዋል። በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ የተገኙ ትዕምርቶች ውስጥ ሴትነት ከመውለድ፣ ከውበት እና ከገርነት አንፃር ሲታይ፤ ወንድነትን በሚያመላክቱ ትዕምርቶች ደግሞ የጥንካሬ፣ ድፍረት እና ስልጣን እሳቤዎች ታይቶባቸዋል።እነ Eagly(2000)፣ Blakemore(2009)፣ Wienclaw(2011) እና Eisenchlas(2013) እንደሚያስረዱት እንደነዚህ አይነት መገለጫዎች ወንዶችን ከገቢ አመንጪነት እና አቅራቢነት እንዲሁም ሴቶችን ደግሞ ከተንከባካቢነት ሚናዎች ጋር የሚዛመዱ ናቸው።። በአጠቃላይ የዶርዜ ማህበረሰብ አባታዊ ስርዓትን የሚከተል፤ በባል ወገን አካባቢ መኖርን የሚፈቅድ፣ በአባት ጎሳ መጠራትን የሚከተል ስርዓት ያለው ማህበረሰብ ነው። አባታዊ በሆኑ ማህበረሰቦች ውስጥ ደግሞ ወንዶች መሪ ወይም ውሳኔ ሰጪ ሴቶች ደግሞ ተንከባካቢ እና ደጋፊ አካላት ጋር የተያያዙ ሚናዎች የተለመዱ እንደሆኑ በተለያዩ ጥናቶችም ተጠቅሷል (Agarwal et al, 2025; Perini, 2022; Thobejane & Khoza, 2014)።

## ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የስርዓተ-ፆታ ሚና በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራ ልማድ አማካኝነት እንዴት እንደተገነባ ማሳየት ነው። በዚህም መሰረት በከበራው ውስጥ የሚመጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ተግባራት እና በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ የሚከወኑ ልማዶች እና ትዕምርቶች ለስርዓተ-ፆታ አገነባብ ያላቸውን አንድምታ ለማብራራት ተሞክሯል።የዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራ ተከታታይነት ባላቸው ስርዓቶች የሚያልፍ ሲሆን እስከ አንድ ወር ከእስራ አምስት ቀን ሊወስድ ይችላል። በእነዚህ ከበራዎች ውስጥ ሴቶች በየደረጃው ካሉ አካላት እውቅናን የሚያገኙባቸው ሆነው ተገኝተዋል። በእነዚህ ከበራዎች ውስጥም ወንዶች በስርዓት መሪነት፣ ፍቃድ ሰጪነት እና አቅራቢነትን በሚመለከቱ ተግባራት ላይ ሲሳተፉ፤ ሴቶች ደግሞ በዋናነት በምግብና መጠጦችን በማዘጋጀት እና በማስተናገድ፣ በማጀብ እና በመደገፍ ተግባራት ላይ መሳተፋቸው ተመላክቷል። እነዚህ ተግባራትም ወንዶች የውሳኔ ሰጪነት ሴቶች ደግሞ በተንከባካቢነት ሚና እንዳላቸው አመላካች ሆኖ ተገኝቷል።

በጋብቻ ከበራዎች ውስጥ ያሉ ተግባራት ከሚገለጡት የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች በተጨማሪ በጋብቻ ሂደቱ ውስጥ የሚከወኑ ልማዶች እና ትዕምርቶች የማህበረሰቡን የስርዓተ-ፆታ ሚና በመገንባት ረገድ ያላቸው አንድምታ ታይቷል። በዚህም መሰረት በጋብቻ ስርዓቶች ውስጥ እንደ ስጦታ፣ ለጋ ቅቤ፣ ኮባ፣ ሆሮርሳ፣ የጫጉላ ቤት አቅጣጫን የመሳሰሉ ቁሶች፤ እንደ መሸከም፣ መንበርከክ እና ማጎንበስ ያሉ ድርጊቶች እና ምርቃት የማህረሰቡን የወንድነት እና ሴትነት እሳቤን ወካይ ሆነው ታይተዋል። እነዚህም በከበራዎቹ ውስጥ ጎልተው በታዩ ዘር የመተካት፣ ውሳኔ የመስጠት፣ የታዛዥነት እና አክባሪነት እንዲሁም የተንከባካቢነት ሚናዎች ውስጥ የወንድ እና የሴት ሚናዎች በተለያየ መልኩ እንደሚታዩ አመላክተዋል። በዚህም መሰረት በአብዛኛው ወንዶች የባለቤትነት፣ የአቅራቢነት እና የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸው ጎልቶ ሲታይ ሴቶች ደግሞ በተንከባካቢነት ሚና ላይ ጉልህ ድርሻ አላቸው።

በዶርዜ ማህበረሰብ የጋብቻ ከበራዎች ውስጥ የታዩ የስርዓተ-ፆታ ሚና አመላካች የሆኑ ሁነቶች፤ ከስራ ክፍፍሉ ጋር በእጅጉ የሚዛመዱ ሆነው ተገኝተዋል። ማህበረሰቡ በተለይ ወንዶች እና ሴቶች ላላቸው ሚና መለያየት ተፈጥሯዊ መላምቶችን ይሰጣል። ዘር ከመተካት እና ከእንክብካቤ አንፃር ያለው ሚናም ከዚህ በትይዩ መታየት ይችላል። ይኸውም ሴቶች ዘርን መሸከም(እርግዝና)፣ መውለድ እና ማሳደግ (ከውልደት እስከ እውቀት) ወንዶች ደግሞ ዘር መስጠት፣ ስርዓት ማስተማር እና ማስያዝ ውስጥ ይሳተፋሉ። ከዚህ በመነሳትም ሴቶች የተሰጣቸውን ዘር ተንከባክበ እና ጠብቆ ለፍሬ በማብቃት መስጠትን፣ ወንዶች ደግሞ የሰጡትን ዘር ሲያፈራ መቀበልን ያመለክታል። በአጠቃላይ በጋብቻ ከበራው ውስጥ የታዩ ተግባራት እና ትዕምርቶች የማህበረሰቡን የወንድነት ልኬት ከመሪነት እና ከባለቤት አንፃር መቃኘታቸው፣ ሴትነትን ደግሞ ከተንከባካቢነት አንፃር ማየታቸው በጥናቱ ተገልጧል።

## ዋቢ ፅሁፎች


Adams, C. J. (2018). The sexual politics of meat. In *Living with contradictions* (pp. 548-557). Routledge.

Agarwal, D., Mohit, Bhuvanasri, P., & Tripathi, S.(2025). Gender Roles: Evolution, Impact and Contemporary Significance. In *Gender Sensitization and Women Empowerment* (pp.11-22). Elite Publishing House

Alesina, A., Giuliano, P., & Nunn, N. (2013). On the origins of gender roles: Women and the plough. *The quarterly journal of economics*, *128*(2), 469-530.

Blakemore, J., Brenbaum, S. and Liben, L..(2009). *Gender Development*. New York: Taylor & Francis Group, LLC.

Bourdieu, P. (2018). Distinction a social critique of the judgement of taste. In *Inequality* (pp. 287-318). Routledge.

Brown, J. K. (1970). A note on the division of labor by sex 1. *American Anthropologist*, *72*(5), 1073-1078.

Burch, R. L. (2019). The wedding as a reproductive ritual. *Review of General Psychology*, *23*(3), 382-398.

Burton, M. L., Brudner, L. A., & White, D. R. (1970). A model of the sexual division of labor. *American Ethnologist*, *4*(2), 227-252.

Carter, M. J., & Fuller, C. (2015). Symbolic interactionism. *Sociopedia. isa*, *1*(1), 1-17.

Chen, J., & Pan, W. (2023). Bride price and gender role in rural China. *Heliyon*, 9(1), 1-9.

Dmitrieva, O. (2016). Traditional Yakut wedding and Algys. *Milli Folklor*, 28(112),154-164.

Durrani, A., & Khan, R. N. A. (2014). Women roles in weddings: ethnography of wedding rituals among Rajput in Punjab, Pakistan. *Eurasian Journal of Anthropology*, *5*(1), 32-45.

Eagly, A. H. and Wood, W.(2021, July 16). Social Role Theory. Retrieved from https://www.researchgate.net/publication/285179532

Eagly, A. H., Wood, W. & Diekman, A. B. (2000). Social role theory of sex differences and similarities: A current appraisal. In T. Eckes & H. M. Trautner (Eds.), *The developmental social psychology of gender* (pp. 123–174). Lawrence Erlbaum Associates Publishers.

Ebo, S. (2022). A Critical Analysis of Gender Roles in Marriage in Igbo African Ontology. *Journal of Gender and Power*, *18*(2), 47-61. r Roles and Expectations

Eisenchlas, S. A..(2013). Gende: Any Change online?. *SAGE Open*,1-11.

Freeman, D. (2002). *Initiating change in highland Ethiopia: Causes and consequences of cultural transformation*. Cambridge University Press

Frobish, T. S. (2004). Ritual as Communication. In Salamone, F. A.(ed.). *Encyclopedia of religious rites, rituals, and festivals*(pp.361-362). ROUTLEDGE, New York; Berkshire Publishing Group.

Gabdrakhmanova, F. H., Zamaletdinov, R. R., & Zamaletdinova, G. F. (2017). Wedding in the History and Culture of the Tatars. *Journal of History Culture and Art Research*, *6*(6), 111-116.

Getaneh M. (2006). The role of women in the household economy: The Dorze case. Addis Ababa, Addis Ababa University. MA Thesis. Unpulished.

Getaneh M. (2014). Betwixt and Between? Culture and women‟s rights in the context of multiple legal and institutional settings, the Dorze case, southwestern Ethiopia. Addis Ababa University PhD Dissertation. Unpulished.

Giuliano, P. (2020). Gender and culture. *Oxford Review of Economic Policy*, *36*(4), 944-961.

Halperin, R., & Olmstead, J. (1976). To catch a feastgiver: redistribution among the Dorze of Ethiopia. *Africa*, *46*(2), 146-164.

Han, J. H. (2004). Food and Rituals. In Salamone, F. A(ed.). *Encyclopedia of Religious rites, rituals, and festivals*(pp.139-143). ROUTLEDGE, New York; Berkshire Publishing Group.

Ickes, W.(1993). Traditional Gender Roles: Do They Make, and Then Break, our Relationships? *Journal of Social Issues*, 49(3),71-85.

Jansen, W. (1997). Gender identity and the rituals of food in a Jordanian community. *Food and Foodways*, *7*(2), 87-117.

Kousaleos, N. (1999). Feminist Theory and Folklore. London, 1996(675-680)

Lindsey, L. L. (2016). *Gender Roles A Sociological Perspective* (6th ed.). New York: Taylor & Francis.

Mamo H. & Getaneh M. (2022). Land Tenure Reforms and Women's Land Rights in Plural 'Legal'and Cultural Settings: A Comparative Study of the Arsii Oromo and Dorze-Gamo, Ethiopia. *Ethiopian Journal of Development Research*, *44*(1), 39-76.

Mathiszig, L. (2015). The dorze weavers of Ethiopia. *Textile*, *12*(2), 180-187.

Morgan D. H.(2007). Marriage. In George Ritzer's (Ed.). *The Blackwell encyclopedia of sociology* (pp. 2789-2791). (Vol. 1479). Malden, MA: Blackwell.

Olmstead, J. (1972). The Dorze House: A Bamboo Basket. *Journal of Ethiopian Studies*, *10*(2), 27-36.

Olmstead, J. (1975). Farmer's wife, weaver's wife: women and work in two southern Ethiopian communities. *African Studies Review*, *18*(3), 85-98.

Pilcher, J. & Whelechan, I. (2004). *Fifty Key Concepts in Gender Studies*. London, Thousand Oaks and New Delhi; SAGE Publicstions Ltd

Pollock, K. T.(2004). Gender Rituals. In Salamone, F. A(ed.). *Encyclopedia of Religious rites, rituals, and festivals* (pp.145-149). ROUTLEDGE, New York; Berkshire Publishing Group.

Ruby, M. B., & Heine, S. J. (2011). Meat, morals, and masculinity. *Appetite*, *56*(2), 447-450.

Sawin, P. E.(1997). Gender. In Thomas A. Green(ed.) *Foklore an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art(pp.*405-408). Santa Barbara, California.

Sidanius, J., Cling, B. J., & Pratto, F. (1991). Ranking and linking as a function of sex and gender role attitudes. *Journal of Social Issues*, *47*(3), 131-149.

Sobal, J. (2005). Men, meat, and marriage: Models of masculinity. *Food and foodways*, *13*(1-2), 135-158.

Terian, S. K.(2004). Marriage Rituals. In Salamone, F. A(ed.). *Encyclopedia of Religious rites, rituals, and festivals* (pp.230-235). ROUTLEDGE, New York; Berkshire Publishing Group.

Thobejane, T. D., & Khoza, J. (2014). Gender role expectations within the institution of marriage. *Journal of Social Sciences*, *41*(3), 455-459.

Thubauville, S. (2012). Brides behind bars: Maale women as captives between tradition and development. *Paideuma*, 213-228.

Turner, R. H. (2002) Role Theory. In Jonathan H. Turner(ed.) *Handbook of Sociological Theory*.(pp. 233-254). New York; Springer.

Wagaye W.(2016). Indigenous Knowledge of Herbal Medicine and Healing Practice Among the Gamo People: The Case of Dorze Dere Southern Ethiopia. Addis Ababa, Addis Ababa University. MA Thesis. Unpulished.

Wienclaw, R. A.(2011). Gender Roles. In *GENDER ROLES & EQUALITY*(pp. 33-40). Pasadena, California: Salem Press

Wood, W. & Eagly, A. H.(2012). Biosocial Construction of Sex Differences and Similarities Behavior. In J. M. Zanna's, *Advances in Experimental Social* (pp. 55-123). Burlington: Academic Press: Elsevier Inc.

Zonabend,F.(2002). Marriage. In Alan Barnard Jonathan's(Ed.). *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology* (pp. 528-530). Routledge.